እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ ያስፈልጋል።
(ዮሐ ፫÷፴-፱-፴)

# ስምዐ ጽድቅ

## ማውጫ


፪ አጫጭር ዜናዎች
፬ መልእክት
፮ ሪፖርታዥ
፱ ቤተ አብርሃም
፲፪ ቃለ መጠይቅ
፲፭ የሕፃናት ዓምድ
፲፯ ትዝብት
፲፱ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ




## ስምዐ ጽድቅ


የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በኅትመት ሚዲያ መምሪያ እየተዘጋጀ በወር ሁለት ጊዜ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ

ጳጉሜን ፭ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም. ተጀመረ



☎ 011-1553555/ 011-1553442
✉ 80078
አዲስ አበባ

የዝግጅት ክፍሉ ኢሜይል
newspaper@eotcmk.org



ምክትል ዋና አዘጋጅ
ወርቅነሽ ቱፋ
ከፍተኛ ሪፖርተር
ካሣሁን ለምለሙ
ሪፖርተር
ምኒልክ ብርሃኑ
የገጽ መልክ (Layout) ዲዛይነርና
ጸሐፊ
ገነት ታደሰ







የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ አብረሃምና በእሳት ቃጠሎ የወደመው የቅኔ ጉባኤ ቤት

# የደብረ ጽዮን ሰላም አርጊው ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ቤተ ያሬድ የቅኔ ጉባኤ ቤት በእሳት ቃጠሎ መውደሙ ተገለጠ

ካሳሁን ለምለሙ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በባሕር ዳር ሀገረ ስብከት የደብረ ጽዮን ሰላም አርጊው ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ቤተ ያሬድ የቅኔ ጉባኤ ቤት መጋቢት ፳፯ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ከለሊቱ ስድስት ሰዓት በተነሣ ድንገተኛ እሳት ሙሉ በሙሉ መውደሙን የቤተ ክርስቲያኗ አስተዳዳሪ መልአከ ጽዮን አባ ወልደ ጊዮርጊስ ተመስገን ከስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ጋር በነበራቸው ቆይታ ገለጡ፡፡

የእሳት ቃጠሎው እጅግ በፍጥነት በመስፋፋቱ በከፍተኛ የሰው ኃይል ቁጥር ለማጥፋት ቢሞከርም መከላከል እንዳልተቻለ የገለጡት ዋና አስተዳዳሪው ከቅዳሴ፣ ከብሉይና ከሐዲሳት ትርጓሜ ጉባኤ ቤቶች ውጭ የቅኔ፣ የድጓና የአቋቋም ጉባኤ ቤቶች መውደማቸውን ተናግረዋል፡፡ ከአራት መቶ በላይ የአብነት ተማሪዎች መኖሪያ የሆኑ የሳር ጎጆዎችን ጨምሮ በውስጣቸው የነበሩ ተማሪዎች የሚማሩባቸውና በግል የጻፏቸው መጻሕፍት፣አልባሳት እንዲሁም መመገቢያ ቁሳቁሶች መውደማቸውን አስተዳዳሪው ካስረዱ በኋላ በተጨማሪም የማኅበራት ቤቶች መውደማቸውን አክለዋል፡፡

የባሕር ዳር ፖሊስ አደጋውን በተመለከተ ሁሉን አቀፍ የወንጀል ምርመራ እያደረገ መሆኑን የተናገሩት ዋና አስተዳደሪው በትምህርት ላይ በነበሩ ሁለት ሺህ ተማሪዎች ላይ ምንም ዓይነት ጉዳት እንዳልደረሰም ገልጠዋል፡፡

ዋና አስተዳዳሪው አክለውም የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ከሆኑት ከብፁዕ አቡነ አብርሃም ጋር በመነጋገር ዐቢይና ንዑስ ኮሚቴ ተቋቁሞ በእሳት ቃጠሎ የወደሙ ጉባኤ ቤቶችን ለመሥራትና የተቃጠሉ ንብረቶችን ለመተካት ጥረት እየተደረገ መሆኑን ተናግረው በዐባይ ባንክ ሒሳብ ቁጥር 2011117964821015 እና በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሒሳብ ቁጥር 1000468707277 እንዲሁም በሌሎች ባንኮች በተከፈተ የሒሳብ ቁጥር ደብረ ጽዮን ሰላም አድርጊው ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ቤተ ያሬድ የቅኔ ጉባኤ ቤት በሚለው ምእመናን ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የባሕር ዳር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ አብርሃም ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቴሌቪዥን ጣቢያ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ ቲቪ) በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት "ቤተ ክርስቲያናችን እየየም ሲደላ በሚያሰኝበት የዘመን ዕራፊ በሆነው ጊዜ ላይ በመገኘቷ በአንዱ ጎን የተወጋችበት የመከራ ችንካር ሳይነቀል በሌላኛው ጎን መወጋቷ የዘመናችን ትዝብት ነው" ብለዋል፡፡

ብፁዕነታቸው አያይዘውም "ባልታወቀ ምክንያት ሙሉ በሙሉ በእሳት የወደመው የባሕር ዳር ደብረ ጽዮን ሰላም አርጊው ማርያም ቤተ ክርስቲያን የአብነት ጉባኤ ቤት የሚያሳየው በሀገራችን ያለውን የችግር ጥግ ነው" ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ብፁዕነታቸው አክለውም በጉባኤ ቤቶች ላይ በደረሰው የእሳት አደጋ ምክንያት የወደሙ የተማሪ መኖሪያ ቤቶችን ለመገንባትና የተቃጠሉ ንብረቶችን ለመተካት የሚደረገውን ጥረት ለማገዝ ቅዱስ ሲኖዶስ የአንድ ሚሊዮን ብር ድጋፍ ማድረጉን አስታውቀዋል፡፡

ጉባኤ ቤቶች የምስጢር፣የጥበብና የፍልስፍና መነሻ በመሆናቸው በእሳት የወደመውን የደብረ ጽዮን ሰላም አርጊው ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ቤተ ያሬድ የቅኔ ጉባኤ ቤት ወደቀደመ ህልውናው ለመመለስ ጊዜያዊ ኮሚቴ ተዋቅሮ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን የተናገሩት ደግሞ የሀገረ ስብከቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ መልአከ ሰላም ኤፍሬም ሙሉዓለም ናቸው፡፡





# መንግሥት በቤተ ክርስቲያን፣በካህናትና በምእመናን ላይ የሚያደረገውን ትንኮሳ እንዲያቆም ተጠየቀ

ካሳሁን ለምለሙ

መንግሥት በቤተ ክርስቲያን፣በካህናትና በምእመናን ላይ የሚያደረገውን ትንኮሳ እንዲያቆም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ መጋቢት ፴ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ባወጣው መግለጫ ጠየቀ፡፡

መንግሥት በተለይ በምእመናን ላይ በየጊዜው እየተፈጸመ ያለው ግድያ፣ ስደትና እንግልት እየተለመደ የመጣ ድርጊት መሆኑን ቅዱስ ሲኖዶስ አስታውቆ “የዚህ ክፉ ድርጊት ማሳያ ደግሞ በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት በአቃቂ ወረዳ ቤተ ክህነት በመካነ ደብረ ስብሐት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን መጋቢት ፳፭ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም በአካባቢው የጸጥታ ኃይሎች ሕይወቱ ያለፈው ወጣት ዘመድኩን አማረ ነው” ብሏል፡፡

ቅዱስ ሲኖዶስ በመግለጫው መጋቢት ፳፭ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም በዕለተ ሰንበት ምእመናን የጸሎት ቅዳሴ ሥርዓትን እየተካፈሉ ባሉበት ወቅት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አምልኮ ከምትፈጽምበት ሃያ ሜትር ባልሞላ ርቀት ላይ “ጸሎትና አምልኮ እንፈጽማለን” የሚሉ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ ወገኖች የምእመናንን ፀጥታ የሚያውክ ተግባር በመፈጸማቸው ምክንያት በተነሳ ብጥብጥ ከጸጥታ ኃይሎች በተተኮሰ ጥይት የወጣቱ ሕይወት እንዳለፈ አስረድቷል፡፡

የግድያ ድርጊቱ ከተፈጸመበት ዕለት ጀምሮ በወረዳ ቤተ ክህነቱና በሀገረ ስብከቱ በኩል ቅዱስ ሲኖዶስ ጉዳዩን ሲከታተል እንደነበረ ገልጦ የቤተ ክርስቲያን አባል የነበረው ወጣት ዘመድኩን በቀለ ያለምንም ጥፋቱ በግፍ “ፀጥታ አስከባሪ ነን” ከሚሉ አካላት በተተኮሰ ጥይት ሕይወቱ ማለፉ በእጅጉ እንዳሳዘነው ገልጧል፡፡

ያለምንም ጥፋት የወጣቱ ሕይወት በግፍ እንዲያለፍ ያደረገው አካል በአስቸኳይ ለፍርድ እንዲቀርብ ያሳሰበው ቅዱስ ሲኖዶስ በመግለጫው የምርመራ ውጤቱ ለሕዝብ እንዲገለጥና ሌሎች የጸጥታ ኃይሎችም ከእንደዚህ ዓይነት እኩይ ድርጊት ተቆጥበው ሕዝብና መንግሥት የሰጣቸውን ኃላፊነት ብቻ በአግባቡ እንዲወጡ ጠይቋል፡፡

ለሁከትና ብጥብጥ ምክንያት እየሆኑ ያሉ የእምነት ተቋማት ከሚያደርሱት ትንኮሳና በቤተ ክርስቲያን ላይ ከሚፈጽሙት የመብት ጥሰት እንዲታቀቡ ቅዱስ ሲኖዶስ በመግለጫው አሳስቦ መንግሥትም በእነዚህ ጠብአጫሪ የእምነት ተቋማት ላይ ያልተቋረጠ የበኩሉን ክትትል እንዲያደርግ እና የምእመናንን ደኅንነትና ሰላም እንዲጠብቅ መልእክት አስተላልፏል፡፡

በመጨረሻም ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን በመሰል ፈተናዎች ግራ ሳይጋቡ ሃይማኖታቸውን ጠብቀውና ከሌላው ጋር በትዕግሥት፣ በጥበብና በፍቅር የመኖር ዕሤታቸውን ይዘው የጀመሩትን የጾምና የሱባኤ ጊዜ እንዲጨርሱ ያስገነዘበው ቅዱስ ሲኖዶስ ለሀገራችን፣ለቤተ ክርስቲያናችንና ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላምና አንድነት አጥብቀው እንዲጸልዩም ጥሪ አቅርቧል፡፡

# ለተቸገሩት ለመድረስ የበጎነት እጆቻችንን እንዘርጋ

ባለፉት ሦስትና ዐራት ዓመታት ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ስትጋፈጥ ቆይታለች። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ‹‹በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ . . .›› (ዮሐ.፲፮፥፴፫) ባለው አምላካዊ ቃል መሠረት ዕለት ዕለት መስቀሉን ተሸክማ እየተጓዘች ክርስቲያኖች በሕይወታቸው የሚገጥማቸውን ፈተና በጽናት እንዲወጡ ቃሉን በማስተማር፣ በማጽናናት፣ ከክፉ እንዲጠበቁ መንገድ በማሳየት፣ ከአምላክ የተቀበለችውን አደራ ስትወጣ ቆይታለች እስከ ዓለም ፍጻሜም የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ይኸው ነው።

ቤተ ክርስቲያን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወገን ከሆኑት ከአይሁድ ጀምሮ ከዐላውያን ነገሥታት፣ ከመናፍቃን ይደርሱባት የነበሩትን ታላላቅ ፈተናዎች በቅዱሳን አባቶችና እናቶች ተጋድሎ አልፋ ከዚህ ዘመን ላይ ደርሳለች። መከራው ግን ዛሬም አልቆመም እንደዘመኑ እና ሁኔታው መልኩን እና አካሄዱን እየቀያየረ ለቤተ ክርስቲያን እና ለምእመናን ፈተና እየሆነ መምጣቱን ቀጥሏል። ቤተ ክርስቲያን ከፊት የተደቀነባትን አንዱን ፈተና በድል ተወጥታ ልጆቿን አጽናንታና አበረታትታ እፎይ ሳትል ሌላ ፈተና ይጠብቃታል።

በተለይ ከጥቅምት ወር ፳፻፲፫ ዓ.ም የጀመረው ዛሬም ድረስ የዘለቀውና ቤተ ክርስቲያንን እየፈተናት ያለው መከራ መልኩ ብዙ ነው። ከዚያም ጊዜ ጀምሮ ብዙ ምእመናን በአክራሪዎች ከቤት ንብረታቸው እንዲፈናቀሉ፣ ከኖሩበት ቀዬ እንዲሰደዱ ሆነዋል። አብያተ ክርስቲያናት ተቃጥለው የተረፉት ንዋያተ ቅድሳት ተዘርፈዋል። ብዙዎች በክርስትናቸው ምክንያት በአሰቃቂ ሁኔታ እየተገደሉ ስለሃይማኖታቸው ሰማዕትነትን ተቀብለዋል።

ቤተ ክርስቲያን በዚህ ሁሉ መከራ ውስጥ ወደ ተጎዱት በመሄድ ስታጽናና፣ በጸሎት ስታስብ፣ ለርዳታ እጆቿን ስትዘረጋ ቆይታለች። አንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከም ዘንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትእዛዝ ነውና በሀገር ውስጥ እና በውጭው ዓለም የሚኖሩ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ከሩቅም ከቅርብም ያሉት በመሰባሰብ በገንዘባቸው፣ በጉልበታቸውና በዕውቀታቸው የፈረሱ አብያተ ክርስቲያናትን መልሶ በመሥራት፣ የተፈናቀሉ ወገኖችን በማቋቋም በአጠቃላይ ዘር፣ ጎሳና ነገድ ሳይለዩ የተጎዱ ወገኖችን ሲረዱ ቆይተዋል። ዛሬም ብዙዎች ተመሳሳይ ርዳታን ይሻሉ፣ ብዙዎች የተዘረጉ እጆችን ይናፍቃሉ። በመሆኑም የትላንትናው መልካም ሥራ ዛሬም እንዲቀጥል የቤተ ክርስቲያን ልጆች በአንድነት ሊቆሙ ይገባል።

ትላንት ቤተ ክርስቲያን ላይ እየደረሰ የነበረው መከራ መልክአ ምድሩን አስፍቶ ቁጥሩን ጨምሮ ዛሬም አላቆመም። ላለፉት ሰባት ወራት በሀገሪቱ ውስጥ ሲካሄድ የቆየው የእርስ በእርስ ጦርነት የብዙዎችን ሕይወት ከመቅጠፉም በላይ በርካቶች ከቤት ንብረታቸው እንዲፈናቀሉ ምክንያት ሆኗል። በዚህ አብያተ ክርስቲያናት እና ገዳማት በሚበዙበት የሰሜኑ ክፍል የተቀሰቀሰው የእርስ በእርስ ጦርነት መጠነ ሰፊ ጉዳት የደረሰባቸው አብያተ ክርስቲያናት እና የቤተ ክርስቲያን ምእመናን መሆናቸው ደግሞ የቤተ ክርስቲያንን ኀዘን እጥፍ ድርብ ያደርገዋል። ይህን የተረዱት ብዙዎች የርዳታ እጃቸውን ዘርግተዋል። ዛሬም እንደዚያ ዓይነቱ ርዳታ እጅግ አስፈላጊ የሆነበት ጊዜ ላይ መሆኑን ሁሉም ሊገነዘበው ይገባል።

በዚያ በክፉ ቀን በመከራው ውስጥ ከምእመናን ጋር በመሆን እና በማስተባበር ያለው ለሌለው እንዲያካፍል በማድረግ በሰሜን ወሎ እና አካባቢው ዘርና ሃይማኖት ሳይለዩ ብዙዎችን ከሞት የታደጉት ብፁዓን አባቶቻችን ለቤተ ክርስቲያን ልጆች ብቻ ሳይሆን ከእምነቱ ውጪ

ለሆኑት ሁሉ አርአያ በመሆናቸው ታሪክ ሲዘክራቸው ይኖራል፡፡ ዛሬም ባለተቋረጠው የሀገሪቱ ችግር ውስጥ የተጎዱ ምእመናንን ለመታደግ ቀድሞ መገኘት የቤተ ክርስቲያን ቀዳሚ ዓላማዋ ነውና ሁሉም የቤተ ክርስቲያን ልጅ ለዚህ በጎ ተግባር መተባበር ክርስቲያናዊ ግዴታ ነው፡፡

ስለ ሀገር ደኅንነት፣ ሰላም ዘወትር በጸሎት የምታስበው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ሕዝብ በረኀብ፣ በበሽታና በጦርነት ሲያልቅ በጸሎት ከመደገፍ ጎን ለጎን ብዙዎችን በመታደግ መጠለያ ያጡትን በማስጠጋት፣ የተራቡትን በማብላትና በማጠጣት የታረዙትን በማልበስ ሀገራዊ ሚናዋ ከፍ ያለ መሆኑን በማሰብ ትላንት ታደርገው እንደነበረው ሁሉ ዛሬም ልጆቿን በመታደግ ግንባር ቀደም መሆን ይጠበቅባታል፡፡ ለዚህም በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭው ዓለም የሚኖሩ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ልጆች ቤተ ክርስቲያንን በመደገፍ የምትሠራውን የሰብአዊ ርዳታ እንድትወጣ ሊረባረቡ ይገባል፡፡

ቤተ ክርስቲያን ትላንት በሚያምነውም በማያምነውም ዘንድ ከሌሎች የእምነት ተቋማት በተለየ መልኩ ያስመሰገናት፣ ትልቅ ቦታን እንድታገኝ ያደረጋት፣ ያስከበራት ልጆቿ በመከራ ውስጥ አልፈው ሌሎችን በመታደግ የፈጸሙት በጎ ሥራ የሚያኮራ እንዲሁም ከአንጋፋዋ ቤተ ክርስቲያን የሚጠበቅ መሆኑ ሊሰመርበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ ሌሎቻችንም በዚያው የበጎነት መንገድ እንድንጓዝ የሚያበረታታ በመሆኑ የተጎዱትን በማሰብ፣ ከችግራቸው እንዲወጡ በማድረግ የአባቶቻችንን ፈለግ መከተል በእግዚአብሔር ዘንድ ጽድቅ ለቤተ ክርስቲያናችን ትልቅ ክብር መሆኑን ሁላችንም በውል ልንረዳው ይገባል፡፡

በአርአያ ሥላሴ የተፈጠሩ ወገኖቻችን እኛ በልተን ስናድር እነርሱ ግን ተርበዋል፡፡ እኛ የሞቀ ቤት ውስጥ ስንተኛ እነርሱ ግን በምድረ በዳ ቀርተዋል፡፡ እኛ የሞቀ ስንለብስ ብዙዎች ታርዘዋል፡፡ በመሆኑም ከንፈር ከመምጠጥ ይልቅ ከቃል ያለፈ በጎ ምግባር ከእኛ ከክርስቲያኖች ይጠበቃል፡፡ ‹‹ወንድም ወይም እኅት ራቁታቸውን ቢሆኑ የዕለት ምግብንም ቢያጡ ከእናንተ አንዱም፦ በደኅና ሂዱ፥ እሳት ሙቁ ጥገቡም ቢላቸው ለሰውነት ግን የሚያስፈልጋቸውን ባትሰጡአቸው ምን ይጠቅማቸዋል? . . . ›› (ያዕ. ፪፥፲፭–፲፯) እንዳለ ቅዱስ ያዕቆብ እንደ ቤተ ክርስቲያናችንም አስተምህሮ በሥራ የተገለጠ እምነት የሚያስፈልግበት ዘመን ላይ ነንና ለዚህ በጎ ተግባር እንትጋ፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ በሁሉም ቦታ ማለት በሚቻል መልኩ ብዙ መፈናቀል፣ ብዙ ስደት፣ ብዙ መራብ፣ ብዙ ሞት የሚታይባት ሀገር መሆኗ ሁላችንንም ሊያሳዝነን፣ ሊያሳስበን ይገባል፡፡ የሚራበው የሚሰደደው፣ የሚፈናቀለው ብሎም የሚሞተው ወገናችን፣ ከአንድ አዳም እና ከአንዲት ሔዋን የተገኘ ወንድማችን መሆኑን በማሰብ ስለ ሀገራችን በመጸለይ ስለወገኖቻችን መራብ ማዘንና ለርዳታ እጃችንን መዘርጋት የሚጽናኑበትንም መንገድ መፈለግ ከእኛ ከኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ይጠበቃል፡፡ እምነታችን በሥራ ይገለጥ ዘንድ የተቸገሩ ወገኖቻችንን ለመርዳት የሁላችንም እጅ ሊዘረጋ ይገባል፡፡

# ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ በብፁዓን አባቶች አንደበት

ክፍል ሦስት

*ትህትናው መኩሪያው*

## ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ
## (ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት)

***የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፬ኛ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ በስደት ከኖሩበት ሀገረ አሜሪካ ሐምሌ ፳፭ ቀን ፳፻፲ዓ.ም ወደ ሀገራቸው ተመልሰው ሦስት ዓመት ከሰባት ወር ቅድስት ቤተ ክርስቲያናቸውን ሲያገለግሉ ቆይተው ባደረባቸው ሕመም በሕክምና ሲረዱ ቆይተው የካቲት ፳፬ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም አርፈው መጋቢት ፩ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ሥርዓተ ቀብራቸው በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን መፈጸሙ ይታወሳል፡፡ ከቅዱስነታቸው ጎልፈት ጋር ተያይዞ ከጠቅላይ ሚንስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ ጀምሮ የተለያዩ የመንግሥት ከፍተኛ ኃላፊዎች፣ አምባሳደሮች የአኃት አብያተ ክርስቲያናት አባቶች ጥልቅ ኀዘናቸውን ገልጸዋል፡፡ አንባብያን እነዚህን የተለያዩ አካላት የኀዘን መግለጫዎች ባለፉት ሁለት ተከታታይ እትሞች ማስነበባችን ይታወሳል፡፡ በሦስተኛው እና በመጨረሻው እትም ቅዱስ ፓትርያርኩን ጨምሮ ብጹዓን አባቶች ስለ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ የሰጡት ምስክርነትና የኀዘን መግለጫ እንደሚከተለው ቀርቧል፡-***

ቅዱስነታቸው ይህችን ቤተ ክርስቲያን እድሜያቸውን በሙሉ አገልግለዋል፡፡

አራተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ለብዙ ዓመታት በብፁዕ ወቅዱስነታቸው ቤተ ክርስቲያናችንን ሲያገለግሉ በክህነታቸው፣ በፓትርያርክነታቸው በሀገር ቤትና በመላው ዓለማት ብዙ አገልግሎት የፈጸሙ ታላቅ አባት ናቸው፡፡



## መርቆሬዎስ መርቆሬዎስን ወሰደ፤ ይህ ራሱ የክብር ምልክት ነው፡፡
### (ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ (የሰሜን ሸዋ ሰላሌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ)

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አራተኛው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ በሞተ ሥጋ ተለይተውናል ኀዘኑ የመላ ኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ምእመናን፣ ካህናት፣ የሁሉም ኀዘን ነው፡፡ ይህ ኀዘን በውጭና በውስጥ ያሉ ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ሁሉ የሚያዝኑት ኀዘን ነው፡፡ ቅዱስነታቸው ዕድሜያቸውን በሙሉ ከሕፃንነታቸው ጀምሮ እስከ ዕረፍታቸው ቤተ ክርስቲያናቸውን አገልግለው ባርከው ቀድሰው ናዝው አስተምረው ያረፉ ታላቅ አባት ናቸው፡፡ ብፁዕ ወቅዱስ አባታችንን እግዚአብሔር አምላክ በመንግሥቱ ይቀበልልን፣ ከቅዱሳን ሰማዕታት ከቅዱሳን መላእክት ጋር ነፍሳቸውን ይደምርልን፡፡



## ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ (የምሥራቅ ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ)

ቤተ ክርስቲያናችን ዕለት እረፍታቸውን ስታስብ ታላቅ ኀዘን ይሰማታል። ይህ ኀዘን የቅዱስ ሲኖዶስ፣ የሊቃውንት፣ የካህናት የድኅ ባለቤቶች በአጠቃላይ ለቤተ ክርስቲያን ታላቅ ኀዘን ነው። የቤተ ክርስቲያን ኀዘን ብቻ ሳይሆን የሀገርም ኀዘን ነው።

እኚህ ታላቅ አባት ብዙ ፈተና ብዙ መከራም ያሳለፉ አባት ናቸው። ትዝ ይለኛል ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ በመኪና አደጋ ሲያርፉ በዋዜማ ሦስት ቀን አካባቢ ሲቀር በዋዜማው ወደዝዋይ ገዳሙ ላይ መጥተው ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ በሕይወት እያሉ ተሰናብተዋቸው ነበር። እንደሚያርፉ በመንፈስ ተረድተው ገዳሙን ባርከው ትንቢት በራእይ እግዚአብሔር ገልጾላቸዋል ይመስለኛል በወቅቱ ሂደው ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስን አብረን እንሂድ ወደ አዲስ አበባ ልወስድዎት ነው የመጣሁት ሲሏቸው ‹‹እኔ ሕፃናት አንባ ፕሮግራም አለኝ ይፍቀዱልኝ ቢሆን ቅዱስነትዎ እዚያ አብረውን ቢሄዱ ጥሩ ነበረ ነገር ግን እዚህ መጥተው ስለጠየቁን ክብር ይስጥልን›› ብለው ምስጋና እንዳቀረቡላቸው ትዝ ይለኛል። ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ በመኪና አደጋ ሲያርፉ አባቶችን አስከትለው መጥተው እንዳከበሩአቸው ትዝ ይለኛል።

ቅዱስነታቸው ወደ ሀገራቸው መጥተው ከዚህም ብዙ አገልግለው በዚሁ አገልግሎት ላይ እያሉ ማረፋቸው የቤተ ክርስቲያናችን ክብር ስለሆነ በጋራ የምንጋረው የሁላችን ኀዘን፣ የቅዱስ ሲኖዶስ ኀዘን ነው። ቤተ ክርስቲያናችን እግዚአብሔር ያጽናት፣ ቅዱስ ሲኖዶስም እግዚአብሔር ያጽናው ሁላችንንም እግዚአብሔር ያጽናን።

ቅዱስነታቸውን ሊቀ ጳጳስ ሳሉ ጀምሮ በቅርበት ባላቃቸውም በአገልግሎታቸው፣ በታሪካቸው አውቃቸው ነበረ። ከእርሳቸው ጋር በደንብ የመተዋወቅ እድል የገጠመኝ ፓትርያርክ ከሆኑ በኋላ ነው። ቅዱስነታቸው፣ እጅግ ትጉህ ቆፍጣና አባት ናቸው መሆን ያለበትና የሌለበት ነገር ‹‹ይሆናል ወይም አይሆንም›› በአንድ ቃል ነው የሚወስኑት በዚህ በደንብ አድርጌ አውቃቸዋለሁ።



## ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ (የምዕራብ ጎጃም ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ)

ማረፋቸውን የሰማሁት ጥዋት በ፳፰ ቀን ነው። ውዳሴ ማርያም እየደገምኩኝ ነበር። ጸሎታ ለማርያም ወስእለታ ለአቡነ መርቆሬዎስ ይዕቀቦ እመአ ተወልዳ እያልኩኝ አሁን ያሉትንም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ እንዲሁ እያልኩኝ ስጸልይ ሃብተ ማርያም የሚባል ልጄ ነው የነገረኝ። ማረፋቸውን ስሰማ በጣም ደነገጥኩና ከባድ ሃዘን ተሰማኝ። መቼም አንድ ቅዱስ አባት ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ በጣም ያስደነግጣል። በተለይ እንደርሳቸው ያለ ቅዱስ አባት።

ቅዱስነታቸው በሁለመናቸው መልካም፣ ቅዱስ አባት፣ መካሪ፣ አስተማሪ፣ የሁሉም አባት፣ የትሕትና አባት፣ ምሁር፣ ሊቅ ነበሩ። በልጅነት ዕድሜያቸው እየተዘዋወሩ ይማሩ ነበርና ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ነው የምንተዋወቀው። በቅኔ ቤቱ፣ በዜማውም ቤት አብረን ተምረናል። የበግ ደበሎ ለብሰን ‹‹በእንተ ስማ ለማርያም ስለቸሩ እግዚአብሔር›› ብለን ነው አብረን የተማርነው፤ አብረንም አገልግለናል። በጣም ጠንካራ፣ የትህርምት አባት ነበሩ። በአብነት ትምህርት ቤትም ከእርሳቸው ጋር ብዙ ትዝታ አለኝ። የተሻገርነው ወንዝ፣ የተጓዝነው ጉዞ፣ የለመነው ልመና ያ ሁሉ ትዝ ሲል በጣም ነው የሚያስለቅሰው፤ ምን ብዬ እናገራለሁ?

‹‹ውሎ ውሎ ከቤት ኑሮ ኑሮ ከመሬት›› እንደሚባለው የቅዱስነታቸው ዕረፍት በሀገራቸው ላይ በመሆኑ ትልቅ ዜና ነው፤ ትልቅ ታሪክም ነው። መጽሐፍ የሚለው ‹‹ የሰው ልጅ የትም ሀገር ሲሰራ ኑሮ የትም ሲጓዝ ውሎ ኋላ በመጨረሻ በርስቱ በሀገሩ ላይ መቀበሩ በጣም መልካም ነው።›› እርሳቸው በመጨረሻው በፈቃደ እግዚአብሔር ወደ ቅድስት ሀገራቸው ወደ ኢትዮጵያ መጥተው እነሆ በክብር ማረፋቸው ደስ ያሰኛል። ወደዚያ ዓለም በመጠራታቸው በጣም ደስ ነው የሚለው። ከእኛ በመለየታቸው ደግሞ ከድንጋይ የከበደ ከበረዶ የቀዘቀዘ ኀዘን ተሰምቶናል። እግዚአብሔር አምላካችን ከበረከታቸው ያድለን፣ እግዚአብሔር አምላካችን ከሁላችን ጋር ይሁን፣ ከብርሃነ ትንሣኤውም በሰላም ያድርሰን፣ የያዝነውንም ጾም ደግሞ በሰላም ፈጽመን ለብርሃነ ትንሣኤው ደርሰን ደስ እንዲለን ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን። የአባታችንንም ነፍስ በሐዋርያት አጠገብ፣ በቅዱሳን አጠገብ ያኑርልን፤ በረከታቸው ይድረሰን፤ እግዝእትነ ወላዲተ አምላክ በረድኤቷ አትለየን አሜን።



# ‹‹ቅዱስነታቸው እንደ አንድ መናኝ እንጂ እንደ ፓትርያርክ አልኖሩም›› ብፁዕ አቡነ አብርሃም (የባሕር ዳር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ)

ብፁዕነታቸው አሜሪካን በነበሩበት ጊዜ ሀገራቸውን እንደሚፈልጉ፣ ወደ ሀገራቸው ገብተው ገዳም ላይ ተወስነው መኖር እንጂ በሰው ሀገር በስደት መኖር እንደማይፈልጉ፤ ከሁሉም ነገር ርቀው በጸሎት ብቻ ተወስነው እግዚአብሔርን እየጠየቁ መኖር እንደሚፈልጉ፤ የቤተ ክርስቲያንን አንድነት እንጂ ልዩነት ጨርሶ የማይፈልጉ አባት እንደ ነበሩ ይታወቃል። ይህም ነው ቅዱስነታቸው ወደ ሀገር ቤት የሚመጡበት መንገድ እንዲመቻች መነሻ የሆነው።

በመሆኑም ቅዱስነታቸው ላለመናገር ወስነው፣ ሁሉን ነገር ትተው ይህችን የተመረጠች ቀን ለማየት እግዚአብሔር ፈቅዶ እሳቸውም ሀገራቸው ገብተው በሀገራቸው በወገናቸው መካከል መቃብራቸው ዕረፍታቸው እንዲሆን እግዚአብሔር የፈቀደላቸውን ጊዜ ለመጠበቅ ዝምታን የመረጡ አባት እንደሆኑ ነው የማምነው።

ብፁዕነታቸው በስደት ሀገር እንደ አንድ መናኝ እንጂ እንደ አንድ ቅዱስ ፓትርያርክ ተመችቷቸው አልኖሩም። ሁሉን ነገር ትተውት የኖሩ አባት ናቸው። የራሳቸው የሆነ ነገር የሌላቸው ሁል ጊዜ እንደ አንድ መንገደኛ፣ እንደ አንድ ተጓዥ በትንሽ ሻንጣ ልብሶቻቸውን አስቀምጠው፤ በአመጋገብም ሁሌም አንድ ዓይነት ምግብ ሲመገቡ የኖሩ አባት ናቸው በአጠቃላይ በጸሎታቸው፣ ሁሉን መናቅን፣ ከንቱነትን፣ የሁሉ ባዶነትን ያስረዱን፣ ያስተማሩን አባት ናቸው።

በመጨረሻም የሁሉ አባት ናቸውና በማረፋቸው የሚሰማኝ ኀዘን ጥልቅ ነው። ምንም እንኳን ለእርሳቸው ይህ ዓለም ባይደላም ‹‹መንኮሰ ሞተ›› ቢሆንም ከዚህ ዓለም ፍላጎት ከተለዩ ብዙ ጊዜያቸው ቢሆንም ከዚህ ቢቆዩ ለሌላው፣ ለሀገር ይጸልያሉ የሚለውን ሳስብ አዝናለሁ፤ በሌላ ምልኩ ደግሞ የእርሳቸውን ሥቃይ፣ ፈተና፣ አኗኗር ሳይና ሳስብ ደግሞ በሰዓቱ በክብር ወደ እግዚአብሄር፣ወደ ተሻለው ዓለም መጠራታቸው ደስ ያሰኛል።



# ‹‹ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ የዝምታ አባት ናቸው ያረፉትም በዝምታ ወቅት ነው›› ብፁዕ አቡነ ናትናኤል (የምዕራብ ሸዋ፣ የምሥራቅ ወለጋ እና የሆሮ ጉድሩ ወለጋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ)

ብፁዕነታቸው በሥጋ ከእኛ በመለየታቸው አዝነናል፤ ኀዘናችን እንደ ሰው ሰውኛ፣ እርሳቸውም ሰው በመሆናቸው እኛም ሰው በመሆናችን እናዝናለን፣ ቤተ ክርስቲያን ታዝናለች፣ ምዕመናን ያዝናሉ እንዲህ ስንል ግን ተስፋ በመቁረጥ አበቃ፣ አለቀ፣ደቀቀ ብለለን አይደለም። እርሳቸው የሄዱት ወደ አባታቸው ወደ አምላካቸው ወደ ፈጣሪያቸው ነው፤ ከምስጋና ወደ ምስጋና ነው የተሸጋገሩት። ሐሰት ከሚነገርባት፣ አድሎ ካለባት፣መለያየት መከፋፈል ካለባት፣ ድካም ካለባት ዓለም ተለይተው ድካም ወደሌለበት፣ ሐሰት ወደማይነገርበት፣ እውነት ወደሚኖርበት፣ አድሎ መከፋፈል ወደሌለበት ወደ አባታቸው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ነው የሄዱት።

እንደሚታወቀው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ የዝምታ አባት ናቸው ያረፉትም በዝምታ ወቅት ነው፤ አሁን እንደ ቤተ ክርስቲያናችንና እንደ ሃይማኖታችን ሥርዓት የጫጫታ ወቅት አይደለም፣ የሁካታ ወቅትም አይደለም፤ የቤተ ክርስትያናችን አገልግሎት እንኳን ከበሮ አይመታበትም፣ ጸናጽል አይጸነጸልበትም። ወቅቱ የጾም ወቅት ስለሆነን ንግግራችን ከእግዚአብሔር ጋር የሚሆንበት፣ ስለ ኃጢአታችን ሥርየት የምንለምንበት፣ ይቅርታ የምንጠይቅበት፣ ስለሀገራችን ሰላም የምንጸልይበት ወቅት ነው። አሁን በአገራችን ላይ ያለው ሁኔታ የሚታወቅ ነው በየአቅጣጫው የሰላም ዕጦት መኖሩ የሚታወቅ ነው። ስለዚህ ያንን እያሰብን መጸለይ ይገባናል፤ የቅዱስነታቸውንም ዕረፍታቸውን ስናስብ በእንደዚህ ዓይነት ነው ማሰብ ያለብን።



# ሊቅነትን ከትሕትና፣ ጸሎትን ከትዕግሥት አጣምረው የያዙ እውነተኛ አባት

ካሳሁን ለምለሙ

**ክፍል ሁለት**

***የተወደዳችሁ አንባብያን የዚህን ጽሑፍ የመጀመሪያ ክፍል ከዚህ በፊት በነበረው እትም ላይ ማቅረባችን ይታወሳል። ሁለተኛውንና የመጨረሻውን ክፍል ደግሞ እነሆ፦***



ብፁዕ አቡነ ኤፍሬም

ከዚያ በኋላም በክቡር ሊቀ ሊቃውንት ነሲቡ ታፈሰ መልካም ፈቃድ የወንዶ ገነት ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን የበላይ ጠባቂ ሆነው አገልግለዋል። በግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ መልካም ፈቃድ በደብረ በግዕ አቡነ ሕፃን ሞዐ ጥንታዊ ገዳም በልቅና ተሹመው የተጎሳቆለውን የቤተ ክርስቲያኑን ገጽታ አድሰዋል፣ የጎደሉ ንዋየ ቅድሳትንም አሟልተዋል፤ይዞታን በማስከበርም አባታዊና ሃይማኖታዊ ኃላፊነታቸውን በብቃት ተወጥተዋል። ከጥቅምት ወር ፲፱፻፷፱ ዓ.ም ጀምሮ በማኅበረ ካህናቱ፣በደቀ መዛሙርቱና በሕዝበ ክርስቲያኑ ዘንድ በከፍተኛ ድምፅ ተመርጠው በታዕካ ነገሥት በአታ ለማርያም ገዳም ሊቀ ሊቃውንት ተብለው ከተሾሙ በኋላ ገዳሙና የሊቃውንት መፍለቂያ የሆነው መንፈሳዊ የካህናት ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት በጊዜው የነበሩባቸውን ችግር ተቋቁመው በብቃት አስተዳድረዋል።

ብፁዕነታቸው ለዘመናት ያካበቱተትን ዕውቀት፣ ትጋት፣መንፈሳዊ ሕይወትና ብቃት በማየት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሦስኛው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት በአንብሮተ ዕድ ጥር ፩ ቀን ፲፱፻፸፪ ዓ.ም የአርሲ ሀገረ ስብከት ሊቃ ጳጳስ ሁነው ተሹመዋል። በዚህ መሠረት በአርሲ ሀገረ ስብከት ከ፲፱፻፸፪ እስከ ፲፱፻፸፫ ዓ.ም ድረስ ብዙ መንፈሳዊ፣ ማህበራዊ እና ሐዋርያዊ አገልግሎቶችን ፈጽመዋል። ከዚያም በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ መሠረት በጽጽስና ያገለግሉበት ከነበረው አርሲ ሀገረ ስብከት ተዛውረው የትግራይ ክፍለ ሀገር ሊቀ ጳጳስ በመሆን እስከ ፲፱፻፺ ዓ.ም ድረስ አገልግለዋል። በትግራይ ክፍለ ሀገር በአገልግሎት በነበሩበት ወቅት ሕዝቡን በመምከር፣ በመርዳት፣ በማስተማርና ያዘነውን በማጽናናት የመከራ ጊዜያትን በትዕግሥትና በመንፈሳዊ ጥበብ እንዲያልፍ በማበርታት ሁሉን አቀፍ አባት አሰብሏቸዋል፤ በሁሉም ዘንድ ተወዳጅነት፣ ሞገስና ክብርንም አስገኝቶላቸዋል።

በተለይም በዕድሜያቸው መግፋት ምክንያት በእርግና ላይ የነበሩን ብፁዕ አቡነ ዮሐንስን በአባትነት አክብረውና አስፈላጊውን ሁሉ እያደረጉ በመንከባከባቸውና ትሕትናቸውን በተግባር በማሳየታቸው በመላው ካህናትና ሕዝበ ክርስቲያን ዘንድ ተወዳጅነት፣ አድናቆትና ክብር ተችሮአቸዋል። ቅዱስ ሲኖዶስ የካቲት፩ቀን ፲፱፻፺ ዓ.ም አዲስ ባወጣው የአህጉረ ስብከት መዋቅር ማሻሻያ መሠረት ከየካቲት ፲፩ ቀን

፲፱፻፩ ዓ.ም ጀምሮ ብፁዕነታቸው የሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሆነው እንዲሠሩ ተመድበው፣ በዚህም ወቅት በርካታ መንፈሳዊ፣ማኅበራዊ፣ ሐዋርያዊና አያሌ ተግባራትን አከናውነዋል፡፡

ሀገረ ስብከቱ አዲስ በመሆኑ ምክንያት መንበረ ጵጵስና ስላልነበረው በደብረ ብርሃን ቅድስት ሥላሴ ሰንበት ትምህርት ቤት አዳራሽ ጀርባ ትንሽ ክፍል ውስጥ አገልግሎታቸውን ጀመሩ፡፡ ዳሩ ግን ብፁዕ አቡነ ኤፍሬም “ጸሎታቸው ተሰሚ፣ መሥዋዕታቸው ጉዳይ ፈጻሚ” ስለነበር ከትዕግሥታቸውና ከትሕትናቸው ጋር በረድኤተ እግዚአብሔር እየታገዙ ለሀገረ ስብከቱ ደረጃውን የጠበቀ መንበረ ጵጵስናና ጽሕፈት ቤት አሠርተዋል፡፡ ሌላውና ትልቁ አገልግሎት ብፁዕነታቸው በሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት በነበሩበት ወቅት ለሁሉም መንፈሳዊ አገልግሎት ትልቅ መንፈሳዊ መሣሪያና የቤተ ክርስቲያን የጀርባ አጥንት የሆነውን የስብከተ ወንጌል አገልግሎት እንዲስፋፋ እና ሰበካ ጉባኤ እንዲጠናከር አድርገዋል፡፡ በየወረዳውና በየአጥቢያው እየተዘዋወሩ በማስተማርና መምህራን በተለያዩ አካባቢዎች ተዘዋውረው እንዲያስተምሩ በመመደብ እንዲሁም በርካታ ሰባክያነ ወንጌል በመንፈሳዊ ኮሌጆች ውስጥ ሠልጥነው ቤተ ክርስቲያንና ምእመናንን እንዲያገለግሉ ለማድረግ በርካታ ደቀ መዛሙርትን ወደ ኮሌጆች ልከው ካሠለጠኑ በኋላ በአገልግሎት እንዲሰማሩ አድርገዋል፡፡

ቤተ ክርስቲያንን በአስተዳደርና በምጣኔ ሀብት ራሷን ለማስቻል በወጣው “የቃለ ዐዋዲ” ደንብ መሠረት ሰበካ ጉባኤ እንዲቋቋም ዕለት ዕለት ክትትል በማድረግ፣ ሰንበት ትምህርት ቤቶች በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ተቋቁመው ወጣቶች በሃይማኖትና በምግባር ትምህርት ተኮትኩተው እንዲያድጉና ቤተ ክርስቲያንን እንዲያገለግሉ ዘርፈ ብዙ ጥረት አድርገዋል፡፡ ሁሉን አቀፍ የራስ አገዝ የልማት ሥራም በየዓይነቱ በቤተ ክርስቲያን እንዲለመድ፣ እንዲሠራና ውጤትም እንዲያሳይ አድርገዋል፡፡ ብፁዕነታቸው በሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት የሚገኙ ታሪካዊና ጥንታዊ ገዳማትና አድባራት ቅርስነታቸው ተጠብቆ ለትውልድ እንዲሻገሩ በአግባቡና ዘመኑ በሚፈቅደው ስልትም ተመዝግበው እንዲጠበቁ እንዲሁም በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋ እንዳይበላሹና እንዳይጎሳቆሉ ደረጃቸውን የጠበቁ ቤተ መጻሕፍትና ሙዚየም አሠርተዋል፤ ያልተሠራላቸውም በአግባቡና በጥንቃቄ እንዲጠበቁ አድርገዋል፡፡ የዚህ ተግባራቸው እውነተኛ ማሳያ የሚሆኑት ደግሞ የሸንኮራ ደብረ መንክራት ቅዱስ ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያን፣ የጻድቃኔ ደብረ ምጥማቅ ቅድስት ማርያም፣ የጻድቃኔ ማርያም አንድነት ገዳምና የብሔረ ሕያዋን ሳማ ሰንበት መድኃይኔ ዓለምና አቡነ ተክለሃ ይማኖት ገዳም፣ የጣርማ በር ቅዱስ ጊዮርጊስና የመንዝ መሐል ሜዳ ቅዱስ ሚካኤል ካቴድራል፣ የዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዐደባባይ ናቸው፡፡

ለዘመናት የቤተ ክርስቲያን ይዞታ ሆኖ በማገልገል የመስቀል ደመራና የጥምቀት በዓላት ማክበሪያ ቦታ የሆነውን የዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዐደባባይ ታሪካዊነቱና ጥንታዊነቱ እንደተጠበቀ በሕጋዊ መንገድ በቤተ ክርስቲያን ስም የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ አሠርተዋል፡፡ በዚሁ ቦታ ላይ ከዋናው መንገድ በኩል የሀገረ ስብከቱ ማእከል ሆኖ እንዲያገለግል በማሰብ የሸንኮራ መጥመቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስን፣ የደብረ ምጥማቅ ቅድስት ማርያምንና ጻድቃኔ ማርያምን በአንድነት በማደራጀት ለቤተ ክርስቲያን የሀብት ምንጭ እንዲሁም ለደብረ ብርሃን ከተማ ደግሞ መገለጫ የሆነ ዘመናዊ ሕንጻ አሳንጸዋል፡፡ ብፁዕነታቸው በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ መሠረት በጸሎትና በቡራኬ ብቻ እንዲወሰኑ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ በሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት ብቻ ከስድስት መቶ በላይ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት እንዲተከሉ፣ ንዋየ ቅዱሳትም እንዲሟሉላቸው አድርገዋል፡፡

ብፁዕነታቸው ነባር የሆኑ የአብነት ትምህርት ቤቶችም ተጠናክረው እንዲቀጥሉ፣ አዳዲስ ጉባኤ ቤቶች እንዲከፈቱ ከግል ደመወዛቸው ጭምር ለመምህራንና ለተማሪዎች በየወሩ ድጎማ እያደረጉ መምህራንን አበረታተው አዳዲስና ነባር አገልጋዮች እንዲተኩ አድርገዋል፡፡ ብፁዕነታቸው በዚህ ዘመን ተሻጋሪ በሆነ ራዕያቸው የበጎ አድራጎት ሥራ እንዲስፋፋ መልካም አርአያ ሆነው በቀጥታም በተዘዋዋሪም ከፍተኛ ጥረት ያደረጉ ፍጹም ቅድስና የተመላ ሰብእና

ያላቸው ተወዳጅና ምስጉን አባት ነበሩ። በተጨማሪም የመርሐ ቤቴ ሚዳ መልሶ ማቋቋም፣ የጊና መንገድ ሥራ ፕሮጀክትና፣ የመሐል ሜዳ ሕፃናት ማሳደጊያ ማዕከልን በመገንባት በኩል ከሚመለከታቸው አጋር አካላት ጋር ያደረጉት አስተዋጽኦ ታሪክ የማይረሳው ተግባር ነው። በሀገረ ስብከታቸው ስብከተ ወንጌል እንዲስፋፋ፣ የምእመናን ቁጥር እንዲበዛ፣ የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ደኅንነት እንዲጠበቅ፣ በሕዝቦችም መካከል መቻቻል ተፈጥሮ ሰላም፣ ፍቅርና አንድነት እንዲነግሥ ላበረከቱት አግልግሎት ከተለያዩ የመንግሥትና ሕዝባዊ ተቋማት ዘንድ የምስጋና የምስክር ወረቀት ተቀብለዋል። ብፁዕነታቸው ከሁሉ በፊት ለእናት ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ የሆኑ ንዋያተ ቅድሳትንና ታላላቅ የብራናና የወረቀት መጻሕፍትን አደራጅተው ለግሰዋል። ደብረ ብርሃን ከተማ ለሚገኘው ርእሰ አድባራት ቅድስት ሥላሴ መንበረ ጵጵስናቸው ብቻ ዐስራ ስድስት ልዩ ልዩ የትምህርት፣ የጸሎትና የምርምር መጻሕፍትንና በርካታ ንዋያተ ቅድሳትን በግል ገንዘባቸው ገዝተው አበርክተዋል። ብፁዕነታቸው በሀገረ ስብከታቸው እንዳሉ ከየካቲት ፩ ቀን ፲፱፻፹ ዓ.ም ጀምሮ በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ መሠረት የትግራይ ሀገረ ስብከት ቋሚ አባት እስኪመደብለት ድረስ ደርበው አገልግለዋል። ከታህሣሥ ፩ ቀን ፲፱፻፹፪ ዓ.ም ጀምሮ ሀገረ ስብከታቸውን እንደያዙ የሰሜን ሸዋ ሰላሌ ሀገረ ስብከትንም ደርበውም በአባትነት መርተዋል።

ብፁዕ አቡነ ኤፍሬም በአጠቃላይ በመምህርነት፣ በአስተዳዳሪነት፣ በሊቀ ጳጳስነት ከስልሳ ዐራት ዓመታት በላይ ደከመኝ፣ ሰለቸኝ ሳይሉ እንዲሁም ልዩ ልዩ ተግዳሮቶችን በጸሎታቸው ተቋቁመው የተሰጣቸውን ሐዋርያዊ ኃላፊነትና ከእግዚአብሔር የተቀበሉትን ቤተ ክርስቲያንንና መንጋውን የመጠበቅ አደራ በብቃትና ፍጹም በሆነ መንፈሳዊ ተጋድሎ አገልግለዋል። ብፁዕነታቸው መርሐ መነኰሳትን የጠበቁ፣ መጽዋች፣ የትሕትናና የትዕግሥት ባለቤት በመሆናቸው የግል ጥሪት ማካበትን የናቁ፤ ሊቅነትን ከትሕትና ጸሎትን ከትዕግሥት አጣምረው የያዙ እውነተኛ አባት ነበሩ። የወር ደመወዛቸውን እንኳ ሳይቀር ለአብነት ትምህርት ቤት ማጠናከሪያና ማቋቋሚያ የሚሰጡ፣ ምግብና ልብስ የሌላቸውን ነዳያንና አረጋውያንን በመርዳት የሚታወቁና ምግባረ ሠናይ የሠሩ አባት ሲሆኑ በዕውቀታቸው መክረው፣ ገሥጸው፣ አስተምረው የተጣሉትን ሁሉ ማስታረቃቸው በሁሉ ዘንድ የተመሠከረላቸው ነበሩ። የቅዱስ ወንጌልን ቃል በአርአያነት በገቢር የፈጸሙ በንጽሕናና በቅድስና ቅዱሳን አባቶቻቸውን የመሰሉ መናኝ አባትም ነበሩ።

ብፁዕነታቸው ከነሐሴ ወር ፳፻፱ ዓ.ም ጀምሮ እርግና ስለተጫናቸዉና በልዩ ልዩ ደዌም ስለተፈተኑ ሥጋዊ ድካም እንዳይበረታባቸው በማሰብ በጸሎትና ቡራኬ ብቻ ተወስነው ሀገርንና ሕዝብን እንዲያገለግሉ ቅዱስ ሲኖዶስ በወሰነው መሠረት በሀገረ ስብከቱ ተገቢው እንክብካቤ እየተደረገላቸው ቆይተዋል። ከዚያ በኋላም እርግና ሲጠና ሕመም ሲበረታባቸው በጸሎት፣ በጠበልና በዘመናዊ ሕክምና እየተረዱ ቆይተው በመጨረሻም ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት "ሕያው ሆኖ የሚኖር፣ ሞትንስ የማያይ ሰው ከቶ ማነው" (መዝ.ዳ ፹፰:፵፰) እንዳለው ብፁዕነታቸው የካቲት ፳፪ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም በተወለዱ በ፹፪ ዓመታቸው ከዚህ ዓለም ድካም ዐርፈዋል። ከፁዕነታቸው የአገልግሎት፣ የብትሕውና የጸሎትና ሕይወት ልምድ የምንማረው ጉዳይ በርካታ ነው። ሆኖም ከልጅነት እስከ ዕውቀት ራስን ለሀገርና ለቤተ ክርስቲያን አሳልፎ መስጠት ለነገ የማይባል ተግባር ሊሆን እንደሚገባ እንማራለን። ጥንታዊ አባቶቻችን ፍጹም በሆነ ቅንነት፣ታማኝነትና በአገልጋይነት መንፈስ ላይ ሆነው ቤተ ክርስቲያንን ያለምንም ግላዊ ጥቅም አገልግለዋል። ዘመኑ ያን ያህል የተሟላ ነገር ያልነበረበት ቢሆንም ራሳቸውን ለአገልግሎት የሰጡትን የአባቶቻችን ታሪክ በደኂላ በማየት አሁን ሁሉ ነገር በተሟላበት ሁኔታ ያለን የዚህ ዘመን ትውልድ ቤተ ክርስቲያናችንን በሁሉም ረገድ ልናግዛት ይገባል። በዚህ ዘመን ያለችውን ቤተ ክርስቲያን ከነሥርዓቷ፣ተውፊቷና ጥንካሬዋ ጋር ለቀጣዩ ትውልድ ልናሻግር የምንችለው ጠንካራና ዘመን የማይሽረው ሥራ ስንሠራ ብቻ መሆኑን ልንረዳ ይገባል።

***የብፁዕነታቸው በረከት ይደርብን!!***

# “ገዳማውያን መነኮሳትና አገልጋዮች እየተራቡ በመሆናቸው በኣታቸውን ጥለው እየተሰደዱ ነው”

**ብፁዕ አቡነ በርናባስ (የዋግኽምራ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ)**

*ካሣሁን ለምለሙ*

ሀገራችን ኢትዮጵያ ዕምቅ የሆነ የተፈጥሮ ሀብትና አያሌ አምራች የሰው ኃይል ያላት ሀገር ብትሆንም በሰው ሠራሽና በተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት ዜጎቿ ለረኃብና ለስደት ተጋላጮች ሲሆኑ ይስተዋላል። በተለይ በዚህ ዘመን ሰዎችን ለከፋ ረኃብና ስደት ከሚዳርጉ ሰው ሰራሽ ክሥተቶች መካከል  አንዱ ጦርነት  ነው፡ ፡ ጦርነት የሰውን ልጅ ሁለንተናዊ ማንነት የሚያጠፋ ከመሆኑ ባሻገር የሰው ልጅ በሕይወት እያለ የሚበላው አጥቶ በረኃብ ተሠቃይቶ እንዲሞት የሚያደርግ ክፉ ክሥተት  ነው። በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በተከሠተው ጦርነት ምክንያት በርካቶች ከፍተኛ ለሆነ የረኃብ አደጋ መጋለጣቸው የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው። ከዚህም ጋር ተያይዞ ብዙዎቹ ለሞትና ለበሽታ ተዳርገዋል። በዚህ ወቅት በጦርነቱ ምክንያት ክፍተኛ የረኃብ አደጋ ከተጋረጠባቸው አካባቢዎች መካከል የዋግኽምራ ሀገረ ስብከት አንዱ ነው። በዚህ ሀገረ ስብከት እስካሁን ድረስ በዕለት ጉርስና በዓመት ልብስ የተቸገሩ በርካቶች ናቸው። በረኃብ ምክንያት አረጋውያን ያለ ጧሪ ሕፃናት ያለአሳዳጊ እየቀሩ ነው። የሚመለከተው አካል አፋጣኝ ምላሽ ካልሰጠ ዘመን የማይሽረው ትውልድ የማይረሳው እልቂት ሊከሠት ይችላል። በዛሬው እትማችንም በአካባቢው የተከሠተውን ችግር መነሻ በማድረግ ባልደረባችን ዲያቆን አሻግሬ አምጤ ከሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ከብፁዕ አቡነ በርናባስ ጋር ያደረገውን አጭር ቆይታ እንደሚከተለው አቅርበነዋል። መልካም ንባብ።

**ስምዐ ጽድቅ፡- ከጦርነቱ ጋር ተያይዞ  በዋግኽምራ ሀገረ ስብከት የነበሩ ችግሮች ምንድን ናቸው? ችግሩን ለማቃለል የተወሰዱ ርምጃዎችስ ምን ምን ነበሩ?**

**ብፁዕ አቡነ በርናባስ፡-** በሀገራችን ብሎም በሀገረ ስብከታችን ከተከሠተው ጦርነት ጋር ተያይዞ የነበረው ችግር እጅግ ውስብስብና መጠነ ሰፊ ነው። ባለፉት አራትና አምስት ወራት ብቻ በሀገረ ስብከታችን ስደት፣ ጦርነት፣ እንግልት ረኃብ፣ እስራትና ሌሎች ሁነቶች ተከሥተዋል። ዋግኽምራ አካባቢ ከዚህ ቀደምም የኢኮኖሚ ከፍተኛ ችግር የነበረበትና የአካባቢው ነዋሪም የተሻለ ኑሮ ፍለጋ ወደተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች የሚሰደዱበት ሁኔታ ነበር። በዚህ ዓመት ደግሞ “ከእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ” እንደሚባለው አካባቢው የጦርነት ቀጠና ሆኖ በመቆየቱ ምክንያት ከፍተኛ የሆነ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ምስቅልቅሎች ተከሥተዋል። በተለይ በዚህ ወቅት የሚላስ የሚቀመስ መጥፋቱ በርካቶች አካባቢያቸውን ጥለው በተለያዩ ቦታዎች በሚገኙ ጊዜያዊ የተፈናቃዮች መጠለያ ጣቢያ ውስጥ ይገኛሉ።

ባሉባቸው መጠለያ ጣቢያዎች አልፎ አልፎ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትና ግለሰቦች በተናጠል ከሚያደርጉላቸው አነስተኛ እገዛ ውጭ በዘላቂነት የሚቋቋሙበት ሥራ እየተሠራ ነው ማለት ያስቸግራል። ለጊዜው በትንሹም ቢሆን የነፍስ አድን ሥራ እየተሠራ ቢሆንም በርካቶች ግን እስካሁን ድረስ ለከፍተኛ ረኃብ በመጋለጣቸው ለሞትና ከመግብ እጥረት ጋር ተያይዞ ለሚከሠቱ በሽታዎች ተጋላጭ ሆነዋል።



የዋግኽምራ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ በርናባስ

በማኅበረሰቡ ላይ የተከሠተውን መጠነ ሰፊ ችግር ለመፍታት በሀገረ ስብከት ደረጃ ዐቢይና ንዑስ ኮሚቴ ተዋቅሮ እንቅስቃሴ ሲደረግ ቆይቷል። ይህም ሆኖ የማኅበረሰቡን ችግር በዘላቂነት ለመቅረፍ አልተቻለም።

በጊዜያዊነት የማኅበረሰቡን የኢኮኖሚ ችግር ለመፍታት አሜርካ ሀገር የሚኖሩ አቶ አራጋው ኃይሌ የተባሉ ግለሰብን በማስተባበር አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሽህ ብር ካገኘን በኋላ ከአውሮፓና አካባቢው እንዲሁም ተጨማሪ አራት መቶ

ሽህ ብር ማግኘት የቻልን ሲሆን በሁሉ ገንዘብም እህል ገዝተን ለተቸገሩ ወገኖች አከፋፍለናል፡፡ ከዚያም የአካባቢውን ነጋዴ ማኅበረሰብ “ቀን ሲወጣ” ገንዘቡን እንደምንከፍላቸው በማስገንዘብ ተጨማሪ እህል በዱቤ እንዲሰጡን አድርገን ከአካባቢው ነጋዴ ማኅበረሰብ ከሦስት መቶ ኀምሳ ኩንታል በላይ እህል መሰብሰብ በመቻላችን በድጋሚ ለተፈናቃይ ወገኖች በማከፋፈል ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ከችግራቸው እንዲወጡ አድርገናል፡፡ ገንዘቡ ለነጋዴዎቹ ባለመመለሱም ቤተ ክርስቲያን እስካሁን ድረስ ባለ ዕዳ ሆናለች፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአካባቢው ገበሬ በዓመት ካመረተው እህል የተወሰነ እንዲሰፍር ባዘዝነው መሠረት እያንዳንዱ ገበሬ ሳይሰስት የሚጠበቅበትን አድርጓል፡፡ የገጠር አጥቢያዎች እንደዚሁ ለተቸገሩ ወገኖች እህል እንዲያወጡ በጻፍንላቸው ደብዳቤ መሠረት  አራትና ከዚያ በላይ ኩንታል እህል በማውጣት  ወገናቸውን ከረኃብ የማውጣት አኩሪ ሥራ ሠርተዋል፡፡ መበጠነኛ ሀብት ከተሰበሰበ በኋላም ከዋናው ኮሚቴ ሥር የሚሠራው ንዑስ ኮሚቴው በየአካባቢው ለብሰውና ጎርሰው መኖር የማይችሉትንና ችግር በከፍተኛ ሁኔታ የጠናባቸውን ጦም አዳሪ የኅብረተሰብ ክፍሎች እንዲለዩ ከተደረገ በኋላ ከዘጠኝ ሽሕ በላይ ለሆኑ ወገኖች ርዳታ ቀርቦላቸዋል፡፡

ይህ ተግባር በችግር ላይ የወደቁ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ያስደሰተ እንዲሁም ከሞት ወደ ሕይወት የመለሰ ነበረ፡፡ ለተቸገሩ ወገኖች የተደረገው ድጋፍ ምንም ዓይነት የሃይማኖት፣የዘርና የአመለካከት ልዩነትን ግምት ውስጥ ያስገባ አልነበረም፡፡ በርዳታው በርካታ የሌላ እምነት ተከታይ ወገኖች ጭምር ተጠቃሚዎች ሆነዋል፡፡ ቤተ ክርስቲያን የሁላችንም እውነተኛ እናት በመሆኗ ችግርንና ረኃብን መስፈርት አድርጋ ሁሉንም የሰው ልጆች ያለምንም አድሎ ረድታለች፤ እየረዳችም ትገኛለች፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን የፍትሐዊ እንጅ የአድሎ ምሳሌ አይደለችምና፡፡ ለኅብረተሰቡ ከተደረገው የዕለት ደራሽ ርዳታ በተጨማሪ በየአካባቢው ያሉ የመንግሥት፣ የግለሰቦች ሀብትና ንብረት እንዲሁም የተፈጥሮ ሀብት  ጉዳት እንዳይደርስባቸው ከፍተኛ ጥንቃቄ የተሞላበት ሥራ ስንሠራ ቆይተናል፡፡

ባለን ውስን የኢኮኖሚ አቅም የአካባቢውን የጤና ባለሙያዎች በመንከባከብ ኅብረተሰቡ የተሟላ የጤናና የመድኃኒት አገልግሎት እንዲያገኝ አስችለናል፡፡ በተሠራው ሥራም ነፍሰጡር እናቶችን ጨምሮ በደዌ ዳኛ በአልጋ ቁራኛ ውስጥ የነበሩ ወገኖች ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ ቤተ ክርስቲያናችን በሀገራችን በትምህርት ሚኒስቴርነትና በሕግ አገልግሎት ስትሠራ መቆየቷ ታሪክ ሕያው መስክር ሆኖ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ደግሞ በአካባቢያችን ጦርነት ከተቀሰቀሰበት ጊዜ ጀምሮ በዋግኽምራ ሀገረ ስብከት አንዳንድ አካባቢዎች የመንግሥት መዋቅር በፈረሰበት ወቅት የመንግሥትን ድርሻ ወስዳ ስትሠራ የነበረች የሀገራችን ብቸኛ መንፈሳዊ ተቋም ነች፡፡ በዚያ ጨለማ ወቅት ቤተ ክርስቲያን የሚጠበቅባትን ሁሉ አገልግሎት ለሰው ዘርና ለእንስሳት ጭምር ስትሰጥ ቆይታለች፡፡ ይህ የእናትነት ተግባሯንም በሰላም ጊዜ ብቻ ሳይሆን በችግር ወቅትም ጭምር ፈጥኖ ደራሽ መሆኗን አስመስክራለች፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በጦርነቱ ምክንያት ቤተ ክርስቲያንና ምእመናን ካሳለፉት ችግር አንጻር ምን ቁም ነገር መማር ይቻላል ይላሉ?**

**ብፁዕ አቡነ በርናባስ፡-** በመከራው ጊዜ በማኅበረሰቡ መካከል የነበረው መተሳሰብና አንድነት ከሚገመተው በላይ ከመሆኑ በተጨማሪ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎትና ችግር ቦታ የማይሰጠው ሰው ሁሉ ፊቱን ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመልስ አድርጎታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቤተ ክርስቲያናችን በኢኮኖሚ ለተቸገሩ ወገኖች መድረስ መቻሏ በምእመናን ዘንድ ቤተ ክርስቲያን በችግር ጊዜ መጠጊያ በረኃብ ጊዜ ደግሞ መንፈሳዊና ሥጋዊ ምግብ የሚያገኙባት እውነተኛ የድሆች ቤት መሆኗን እንዲረዱ አድርጋለች፡፡ መደጋገፍና መተሳሰብ ካለ የሚመጣን መከራና ክፉ ዘመን ሁሉ ማለፍ እንደሚቻል የተማርንበት ወቅትም ነው፡፡ ርዳታ ከውጭ ሀገር ከመጠበቅ ይልቅ ራስን መቻል አዋጭ መሆኑንም ተገንዝበናል፡፡ በመከራው ወቅት የተለየ የመተሳሰብና የመረዳዳት ባህል ነበር፡፡ ራሳቸውን መመገብና ማልበስ ለማይችሉ ወገኖች በኢኮኖሚ ጠንካራ የሆኑ የአካባቢው ማኅበረሰብ አንዱ እራት ሲችል ሌላው ምሳ ይችል ነበር፡፡ ይህ ተግባር ሌላኛው የመተዛዘን ገጽታ ነው፡፡ ተግባሩ በሀገራችን ቀድሞ የነበረው የመረዳዳት ዕሤት ጨርሶ እንዳልጠፋ ያስተማረን ሆኖ አልፏል፡፡ ጦርነቱ በአጠቃላይ ብዙ ጥበቦችንና መልካም ነገሮችን አስተምሮን ያለፈ ነው፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በሀገራችን በየአካባቢው እየተከሠተ ያለው እልቂት እንዲቆም ምን ቢሠራ መልካም ነው ይላሉ?**

**ብፁዕ አቡነ በርናባስ፡-** መደማመጥና መግባባት በሀገሪቱ ጠፋ እንጂ ቤተ ክርስቲያንን ጨምሮ ድርጅቶችና ግለሰቦች የሰላም ምክረ ሐሳብ ሲያቀርቡ ቆይተዋል፡፡ ቤተ ክርስቲያን የሀገራችን ዋልታና ምሰሶ መሆኗ በዘመናት በሀገራችን በሚከሠቱ የሰላም መደፍረሶች ምክንያት ለተለያዩ አካላት የሰላም ጥሪ ስታቀርብና ከዚያም አልፋ የአስታራቂነት ድርሻ ወስዳ ስትሠራ ቆይታለች፡፡ በቅርቡ እንኳን በሀገራችን በሰሜኑ ክፍል የተከሠተው ጦርነት እንዳይመጣ ቤተ ክርስቲያን ከአጥቢያ እስከ ቅዱስ ሲኖዶስ ድረስ ከፍተኛ ጥረት አድርጋለች፡፡ የአንድ እናት ልጆች ልዩነታቸውን በመነጋገርና በሐሳብ የበላይነት ብቻ እንዲፈቱ ስትጥር ብትቆይም ሰሚ ጆሮ አስተዋይ ልቡና ባለመኖሩ ጦርነት ተቀስቅሶ በርካታ የሰው ልጆች ለሞት፣ለስደትና ለረኃብ ተዳርገዋል፤የተፈጥሮ ሀብትና ተቋማት ወድመዋል፡፡

ገበሬው እንዳያርስ፣ተማሪው እንዳይማር፣ነጋዴው ነግዶ እንዳያተርፍ እንዲሁም የመንግሥት ሠራተኛው ሕዝብን እንዳያገለግል ሆኖ ቆይቷል፡፡ በዚህም ሀገራችን ካስተናገደችው ውስጣዊ ኢኮኖሚያዊ፣ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ጫና በተጨማሪ

ለታሪካዊ ጠላቶቻችንና ለምዕራባውያን መጫወቻና ማላገጫ ሆናለች። ቤተ ክርስቲያናችን የሰላም መደፍረስ ምክንያት የሆኑትን ለመምከር ሞከረች ግን የሚመከር የለም፤ለመሸምገል ሞከረች የሚሸመገል የለም፤ጦርነት አይጠቅምም ተው ብላለች የሚተው የለም፤አድመጡኝ ብላለች አድማጭም የለምና ለብዙ ምስቅልቅልና መከራ መንሥኤ የሆነው የሰሜኑ ጦርነት ተቀሰቀሰ። ቤተ ክርስቲያን ዕለት ዕለት የሀገርና የሰው ልጆች ሰላም ጉዳይ የሚያሳስባት በመሆኑ አሁንም ቢሆን የሰላም ጥሪ ግጭት ላይ ላሉ ወገኖች ታቀርባለች። ይህንን ጥሪ ተከትሎ ሀገራችን የሰላም ድምጽ የሚሰማባት እንድትሆን እንመኛለን። የሰላም ባለቤት የሆነው ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሀገራችንና በወገኖቻችን መካከል ሰላምን እንዲያመጣና በቸርነቱ እንዲጎበኘን እንማጸናለን። ከጦርነትና ከረኃብ ጋር ተያይዞ የሚመጣ ችግር ለማንም ወገን አትራፊ አይደለምና መንግሥት ይህንን ተረድቶ ሁሉንም የሰላም አማራጮች በመጠቀም በሀገራችን ዘላቂ ሰላምና ልማት እንዲመጣ አበክሮ መሥራት አለበት እላለሁ።

**ስምዐ ጽድቅ፡- እንደ መንፈሳዊ አባት ከዚህ ቀደም የቻሉትን ሁሉ አድርገው ሕዝቡን ከጦርነት እልቂትና ከረኃብ መታደግዎ ይታወቃል፤ አሁንስ ሕዝቡና አገልጋች በምን ሁኔታ ላይ ይገኛሉ?**

**ብፁዕ አቡነ በርናባስ፡-** የዋግኽምራ አካባቢ ማኅበረሰብ ከጦርነት በፊትም ቢሆን በከፋ ድህነት ውስጥ ይኖር የነበረ ሕዝብ ነው። ከግማሽ በላይ የሚሆነው መሬት ለእርሻ ምቹ ያልሆነና ማኅበረሰቡም ትርፍ አምራች የሚባል አይደለም። ለድርቅ ተጋላጭነቱም ከፍተኛ ነው። በዚህ ምክንያት የአካባቢው ማኅበረሰብ በከፋ ድህነት ውስጥ ባለበት ወቅት ነው ጦርነት የተጨመረበት። ጦርነቱም የችግር ስፋቱን ይበልጥ ውስብስብ አደረገው፤በዚህ ሳቢያ በርካቶችን ለሕመም፣ለሞትና ለስደት ዳርጓቸዋል። አካባቢውም ከሀገራችን ሌሎች አካባቢዎች በተለየ ሁኔታ ከመሠረተ ልማትና ከዕድገት ተጠቃሚነት የተገለለ በመሆኑ የንግድ አካባቢያዊ ትስስር እንዳይኖር አድርጎታል። በሀገረ ስብከቱ በርካታ መምህራን፣የአብነት ትምህርት ቤቶች፣ገዳማትና አድባራት ያሉት ሲሆን ሀገረ ስብከቱም አዲስ ሆኖ ከመቋቋሙ ጋር ተያይዞ የራሱ የሆነ ለመንበረ ጵጵስና አገልግሎት የሚውል ሕንጻ ካለመኖሩ ባሻገር ለሀገረ ስብከቱ አገልጋዮች የሚከፍለው ወርኃዊ ደምወዝ እንኳን ተቸግሯል።

በመሆኑም ገዳማውያን መነኮሳትና አገልጋዮች እየተራቡ በመሆናቸው በኣታቸውን ትተው እየተሰደዱ ነው። ገዳማውያንና አገልጋዮች እንዳይበተኑና የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዳይታጎል በርኅራኄና በልግስና የሚታወቀው መልካሙ የኢትዮጵያ ሕዝብ የቻለውን ሁሉ በማድረግ የድርሻውን እንዲወጣ ጥሪ አስተላልፋለሁ።

በችግርና በመከራ ወቅት ያለው ሰው ለሌለው ቢያካፍል መልካምና የጽድቅ መንገድ ጠራጊ ተግባር ነው። አፋጣኝ የሆነ የገንዘብና የዓይነት ድጋፍ ቢደረግልን የተበተኑ አገልጋዮችንና ምእመናን ወደ ቀደመ አካባቢያቸው መሰብሰብ ያስችለን ነበር።

**ስምዐ ጽድቅ፡- በተለያየ ጊዜ ርዳታ ሲመጣ የአብነት ተማሪዎችንና ገዳማትን ተደራሽ አያደርግምና፤ ምን ቢደረግ ነው የእነዚህን አካላት የኢኮኖሚ ችግር ማቃለል የሚቻለው?**

**ብፁዕ አቡነ በርናባስ፡-** ለአብነት ተማሪዎች፣ለገዳማትና አድባራት አገልጋዮች ርዳታ በዋናነት መድረስ የሚችለው በሀገረ ስብከቱ በኩል ሲመጣ ብቻ ነው። እስካሁን ድረስ በሀገረ ስብከቱ በኩል የመጣ ድጋፍ ባለመኖሩ ለአገልጋዮች የምንሰጠው የገንዘብም ሆነ የዓይነት ድጋፍ አልነበረንም። በዚህም የተነሣ ብዙ የአብነት ተማሪዎቻችን የሚኖሩበት ቤት፣የሚለብሱት ልብሳና የሚበሉት ምግብ ለማግኘት ተቸግረዋል። ከምግብ እጦት በተለየ ሁኔታ ሚለብሱት አልባሰት ባለመኖሩ ቀን በፀሐይ ሌሊት በቁር እየተሠቃዩ ይገኛሉ። እስካሁን ድረስ የሁሉንም የአብነት ተማሪዎች ችግር ለማቃለል ባንችልም እንኳን ከበጎ አድራጊ ግለሰቦች በተገኘ ገንዘብ የጥቂት ተማሪዎችን ችግር በከፊል ለማቃለል ጥረት እያደረግን እንገኛለን። ይህንን የተቀደሰ ዓላማ ሁሉም የድርሻው ሊያደርገው ይገባል። ቤተ ክርስቲያናችንም የተማሪዎቻችንን የኢኮኖሚ ችግር ለማቃለል ዘላቂ የሆነ የገቢ ምንጭ ሊኖራት ይገባል። አቅሙ ያላቸው ምእመናን የቤተ ክርስቲያንን የርዳታ ድምጽ በመስማት ምላሽ ሊሰጡ ይገባል። የአብነት ተማሪዎች ለቤተ ክርስቲያናችን ተተኪ አገልጋዮች በመሆናቸው በቀጣይ እግዚአብሔርን አጋዥ አድርገን ችግሮቻቸውን ለመፍታት እንሞክራለን። ሀገረ ስብከቱን ከድህነት የጸዳ ማድረግ ባይቻልም እንኳን ሀገራችን ሰላም ከሆነች ችግሮችን ደረጃ በደረጃ ለመፍታት ዕቅድ ይዘናል።

**ስምዐ ጽድቅ፡- በመጨረሻ ቀረ የሚሉት ነገር ካለ?**

**ብፁዕ አቡነ በርናባስ፡-** ቀሪው ዘመናችን ለሁላችንም የመጽናናትና የመረጋጋት ዘመን እንዲሆንልን እግዚአብሔርን መለመን አለብን። በሀገራችን ብሎም በሀገረ ስብከታችን የደረሰው መከራ መተጋገዝና መተባበር አስፈላጊ እንደሆነ አስተምሮናል። ከረኃብ ነጻ ያልወጡ ወገኖቻችንን ነጻ ለማውጣት የሁላችን ድርሻ ሊሆን ይገባል። በተለይም የገዳማትና የአድባራት አገልጋዮች ዕለታዊ ርዳታ ያስፈልጋቸዋል።

ገዳማቱንና የአብነት ትምህርት ቤቶችን መደገፍ እንድንችልና መምህራን በወንበራቸው ጸንተው ተተኪ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን እንዲያፈሩ ለማድረግ የሁላችንም እገዛ ያስፈልጋል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ አገልጋዮችን ለማቆየትና ለነገዋ ቤተ ክርስቲያን ተተኪ ትውልድ ለማፍራት በዚህ ዘመን ያለን ትውልድ ሁሉ መክፈል ያለብንን ዋጋ ልንከፍል ይገባል። በአጠቃላይ ሀገረ ስብከቱ ችግር ላይ መውደቁን ምእመናንና መላው ኢትዮጵያውያን ተረድተው የድጋፍ እጃቸውን እንዲዘረጉ ጥሪ አስተላልፋለሁ።

# ዐበይት ነቢያት፤ ክፍል አራት ፡- ነቢዩ ዳንኤል

ምኒልክ ብርሃኑ

ልጆች! እንደምን ሰነበታችሁ? አሜን የእግዚአብሔር ስም የተመሰገነ ይሁን እኛ በጣም ደኅና ነን፡፡ ልጆች የሁዳዴ ጾም እንዴት ነበር? አሁን መዋዕለ ጾሙ ሊያልቅ ሁለት ሳምንት ብቻ ቀርቶታል እናንተም ከጾሙ በረከት ስለተሳተፋችሁ ዕድለኞች ናችሁ ቀሪውንም ጊዜ በብርታት መጾም ይገባችኋል እሺ ልጆች በርቱ!

ልጆች! ባለፉት ሦስት ተከታታይ እትሞች ላይ ስለ ዐበይት ነቢያ ታሪክ ፡- ስለ ነቢዩ ሕዝቅኤል፣ ስለ ነቢዩ ኤርሚያስ እና ስለ ነቢዩ ኢሳይያስ ታሪክ በተከታታይ ወደ እናንተ ማቅረባችን ይታወሳል፡፡ አሁን ደግሞ አራተኛውንና የመጨረሻውን ክፍል የነቢዩ ዳንኤልን ታሪክ ይዘንላችሁ ቀርበናል በጥሞና ተከታተሉን እሺ ልጆች!

ልጆች! ከላይ እንደገለጽንላችሁ ነቢዩ ዳንኤል ዐበይት ከሚባሉት ነቢያት አንዱ ነው፡፡ ‹‹ዳንኤል›› የሚለው ስም ‹‹ዳን›› እና ‹‹ኤል›› ከሚሉ ሁለት ቃላት ጥምረት የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም ‹‹እግዚአብሔር ፈራጅ ነው›› ማለት ነው፡፡ ነቢዩ ዳንኤል የዮናኪር የልጅ ልጅ ሲሆን ዮናኪር ደግሞ የንጉሥ ኢዮአቄም ልጅ የሠለስቱ ደቂቅ አባትም ነው፡፡

ልጆች! ናቡከደነጾር ኢየሩሳሌምን በወረራት ጊዜ አባታቸው ዮናኪር ልጆቹን አናንያ፣ አዛርያ፣ ሚሳኤልን እንዲሁም የልጁን ልጅ ዳንኤልን እና ብዙዎቹን የእስራኤል ልጆች ከእነርሱ ጋር ማርኮ ወደ ባቢሎን ወሰዳቸው፡፡ ነቢዩ ዳንኤል ወደ ባቢሎን ከገባ በኋላ ስሙ ‹‹ብልጣሶር›› በሚል ስም ተቀየረ፡፡ ብልጣሶር ማለት በከለዳውያን ቋንቋ “የበዐል መስፍን” ማለት ነው፡፡ አብረውት የተማረኩት ሦስቱ ወጣቶችም ስማቸው ተቀይሮ ሐናንያ የነበረው ሲድራቅ ፣ ሚሳኤል የነበረው ሚሳቅ እንዲሁም ዐዛርያ የነበረው አብድናጎ ተብለው እንዲጠሩ ሆነዋል፡፡

ልጆች! የነቢዩ ዳንኤልንና የሦስቱን ሕፃናት ስም ለምን እንደቀየሩት ታውቃላችሁ? እነዚህ የተቀየሩት ስሞች ከባቡሎናውያን አማልክት ጋር የተቆራኘ ትርጉም ስላላቸው ነው፡፡ ሲድራቅ ማለት ‹‹በፀሐይ አምላክ የተገለጠ››፣ ሚሳቅ ማለት ‹‹በሻቅ›› (የውበትና የመሬት አምላክ) እንዲሁም አብድናጎ ማለት‹‹ የእሳት አምላክ አገልጋይ›› የሚል ትርጓሜ ያላቸው የአማልክት ሥሞች ስለሆኑ ነው፡፡

ልጆች! ነቢዩ ዳንኤልና ሠለስቱ ሕፃናት ወደ ባቢሎን ከተማረኩ በኋላ የተሰጡት ኤስፋዝ ለሚባል ለናቡከደነጾር የጃንደረቦች አለቃ ነበር፡፡ በዚያም የከለዳውያንን ትምህርት ተምረዋል፡፡ (ት.ዳን. ፩፥፩–፯) የተማሩት ስለ እግዚአብሔር ሳይሆን የከለዳውያንን የኮከብ ቆጠራ፣ ሒሳብ፣ አስማት፣ እንዲሁም ሕልም መፍታት የመሳሰሉትን ትምህርቶች ነበር፡፡ ዳንኤልም የባቢሎናውያንን ትምህርት ከተማረ በኋላ በዚያው ሀገር ላይ ተሹሞ በማስተማር፣ ሕልምን በመፍታት፣ መጽሐፍንም በመተርጎም ማገልገል ጀመረ፡፡

ነቢዩ ዳንኤልና ሦስቱ ሕፃናት በትምህርት ቤቱ ውስጥ ለንጉሥ አማካሪነት ሲማሩ የጃንደረቦቹ አለቃ አስፋኔዝ የሚመገቡትን ምግብ እና የሚያርፉበትን መኝታ ከቤተ መንግሥት እንዲያገኙ በንጉሡ ታዞ ነበረ፡፡ ምንም እንኳ እንዲህ ዓይነት እንክብካቤ ቢደረግላቸውም ዳንኤል የእግዚአብሔር ሰው ነውና በአማልክቶቻቸው እንዳይረክስ በልቡ ይጠነቀቅ ነበር፡፡ (ዳን.፩፥፰–፲፫) በመሆኑም የጃንደረቦቹን አለቃ አሳምኖ ከሠለስቱ ደቂቅ ጋር የሚበሉትን ጥራጥሬ እና ውኃ ብቻ እንዲሰጣቸው ለመነ (ዳን.፩፡፰-፲፫)፡፡ የጃንደረቦቹ አለቃ አስፋኔዝም የጠየቁትን ከመረመረ በኋላ እንደጥያቄአቸው ጥራጥሬ እና ውኃ ብቻ እንዲገባላቸው ፈቀደላቸው (ዳን.፩፡፲፬-፲፮)፡፡ ልጆች! እነዚህ ሕፃናት ያደረጉትን አስተዋላችሁ? በሰው ሀገር ላይ ነሰው ሀገር ላይ በምርኮ ቢሆኑም አምላካቸውን እግዚአብሔርን አልረሱትም ጾምን ለመጾም ወሰኑ እንጂ በንጉሥ ቤት የተዳለደ ኑሮ አልተታለሉም፡፡

ልጆች! ነቢዩ ዳንኤልና ሦስቱ ሕፃናት እግዚአብሔርን በማክበራቸው ከሁሉ በላይ ማስተዋልና ጥበብ ተሰጣቸው (ዳን.፩፡፲፯)፡፡ በተለይ ነቢዩ ዳንኤል ሕልም እና ራዕይ የመፍታት ፀጋ ተሰጠው፡፡ ንጉሡ ናቡከደነጾር በአንድ ወቅት መጥፎ ሕልም አይቶ በጣም ተጨንቆ ነበር፡፡ በዚህን ጊዜ የከለዳውያንን አስማተኞች በመጥራት ሕልሙን እንዲፈቱለት ወደ ቤተ መንግሥት ቢያስጠራቸውም ፍቺውን መናገር ግን አቃታቸው፡፡ በዚህን ጊዜ ነቢዩ ዳንኤል ሕልሙንና ፍቺውን ተረጎመለት በዚህም ንጉሡ ስለተደሰተ በባቢሎን አውራጃ ኹሉ ላይና በባቢሎን ጠቢባን ላይ አለቃ አድርጎ ሾመው፡፡ ከእርሱም ጋር የነበሩት ሦስቱ ደቂቅም በባቢሎን ተሾሙ (ዳን.፪ ፥ ፩– ፵፱)፡፡

ልጆች! የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነጾር ከሞተ በኋላ የልጁ ልጅ ብልጣሶር ነግሦ ነበር። እርሱም አባቱ ከኢየሩሳሌም ያስመጣቸውን ንዋየ ቅዱሳት (የቤተ መቅደስ መገልገያዎች) ከተቀመጡበት ግምጃ ቤት አስመጥቶ መኳንንቱና ሚስቶቻቸው እንዲጠጡበት አደረገ። መጠጣት ብቻ ሳይሆን በንዋያተ ቅድሳቱ እየጠጡ ጣዖቶቻቸውን ያመሰግኑ ነበረ። ድንገትም የሰው ጣቶች በሁሉ ፊት ታዩ፤ በንጉሡ ቤት ግድግዳ ላይም ይጽፉ ጀመር ቃሉም ‹‹ማኔ፣ ቴቄል፣ ፋሬስ›› የሚል ነበረ። ንጉሡም ደንግጦ እንደልማዱ አስማተኞችን በመጥራት ጽሕፈቱን እንዲተረጉሙለት ቢያዛቸውም ሊተረጉሙለት አልቻሉም። በዚህን ጊዜ የጽሑፉን ፍቺ ‹‹ማኔ›› ማለት ‹‹እግዚአብሔር መንግሥትህን ቆረጠው›› ማለት ነው። ‹‹ቴቄል›› ማለት ‹‹በሚዛን ተመዝነህ ቀለህ ተገኘህ››ማለት ነው። ‹‹ፋሬስ›› ማለት ‹‹ መንግሥትህ ተከፈለ ፥ ለሜዶንና ለፋርስ ሰዎችም ተሰጠ›› ማለት ነው በማለት የፈታለት ነቢዩ ዳንኤል ነበረ።

ልጆች! ንጉሡ ያደረገውን የድፍረት ሥራ አስተዋላችሁ? የእግዚአብሔርን ቤት የተቀደሰ እቃ ለራሱና ለመኳንንቶቹ መጠጫ በማድረጉ እግዚአብሔር እንዴት እንደቀጣው እና ንጉሡ ብልጣሶር በዚያው ሌሊት ሲሞት እናያለን (ዳን.፭፥፩–፴፩)።

ነቢዩ ዳንኤል በምርኮ ሀገር ቢኖርም ባቢሎንን በመስፍንነት ያገለገለ ጻድቅ ሰው ሲሆን የመጸለይ፣ የመጾም፣ የነቢይነት፣ ሕልምና ራዕይን የመተርጎም ፀጋ ነበረው። በዚህ ፀጋና ጥበብም በባቢሎን ቤተ መንግሥት ውስጥ ሆኖ ሕዝቡን ያገለግል የነበረ ታላቅ ነቢይ ነው። ነገሥታቱ እና መኳንንቱ ጣዖታት የሚያመልኩና ለእነርሱ የሚሰግዱ ቢሆኑም እርሱ ግን አይሰግድም ነበር። ነገሥታቱንና ሕዝቡንም ሳይፈራ ስለእግዚአብሔር ያስተምራቸው ነበረ። ስህተታቸውንም በግልጽ እየነገረ ይገስጻቸው ነበረ። ሁሉንም ፊት ለፊት ስለሚገስጻቸው በቤተ መንግሥት አካባቢ ያሉት በጠላትነት ተነሡበት። የንጉሥ ትእዛዝ ያላከበረ ወደ አንበሶች ጉድጓድ እንዲጣል የሚል አዋጅ አስወጡ። ነቢዩ ዳንኤልም መስኮቱን ወደ ኢየሩሳሌም አቅጣጫ ከፍቶ በቀን ሦስት ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ይጸልይ ነበርና መኳንንቱ ወደ ንጉሡ ቀርበው ትእዛዝህን አላከበረም በቀን ሦስት ጊዜ ወደ አምላኩ ይጸልያል ብለው ከሰሱት በንጉሥ አዋጅ መሠረትም ወደ አንበሶች ጉድጓድ እንዲጣል አደረጉት።

ልጆች! አንበሶቹ ነቢዩ ዳንኤልን የበሉት ይመስላችኋል? አብረን እንከታተል። ንጉሡ በማግሥቱ በጥዋት ዳንኤል ወደተጣለበት ዱድጓድ ሄደ። ወደ ጉድጓዱ ሲቀርብም አንበሶቹ ገነጣጥለው በልተውታል ብሎ ስላሰበ በሀዘን ቃል ‹‹የሕያው አምላክ ባርያ ዳንኤል ሆይ፥ ሁል ጊዜ የምታመልከው አምላክህ ከአንበሶች ያድንህ ዘንድ ችሎአልን?›› አለው። ዳንኤልም ‹‹በፊቱ ቅንነት ተገኝቶብኛልና፥ በአንተም ፊት ደግሞ ንጉሥ ሆይ አልበደልሁምና አምላኬ መልአኩን ልኮ የአንበሶችን አፍ ዘጋ ፥ እነርሱም አልጎዱኝም አለው።

ልጆች! ንጉሡ የዳንኤልን ድምጽ ሲሰማ እጅግ ደስ ብሎት ከአንቦሶቹ ጉድጓድ ውስጥ እንዲያወጡት አዘዘ። እሱንም አሳልፈው የሰጡትን ወደ ጉድጓዱ አስጣላቸው፤ ወደ መንግሥቱ ግዛት ሁሉ ደብዳቤ በመጻፍም በዳንኤል አምላክ እንዲያምኑ ለእርሱም እንዲሰግዱና እንዲፈሩትም ጭምር ሁሉንም የግዛቱን ሕዝብ አዘዘ (ዳን.፮፥፩–፳፰)። እስራኤላውያን ከምርኮ ወደ ሀገራቸው እስከሚመለሱበት ጊዜ ድረስ የኖረው በባቢሎን ነው። ነቢዩ ዳንኤል እስራኤላውያን በምርኮ ባቢሎን የኖሩት ለ፸ ዘመን ነው። ነቢዩ ዳንኤልም ብዙ ካገለገለ በኋላ በ፹፬ ዓመቱ ዐረፈ።

ልጆች! ከነቢዩ ታሪክ የምንማራቸው ታላላቅ ቁምነገሮች አሉ። ነቢዩ ዳንኤል ከሀገሩ ከኢየሩሳሌም ተማርኮ የመጣው በሕፃንነቱ ወራት ቢሆንም እንደባቢሎናውያን ጣዖትን አላመለከም። ይልቁንም የንጉሥን ቤት የጣፈጠ ምግብ እምቢ ብሎ በጥሬ እና በውኃ ብቻ በመጾም እምነቱን በመግለጥ ንጉሡ እና ሕዝቡ እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ ያደረገ ጻድቅ ነው። እንግዲህ ልጆች እኛም ልክ እንደ ነቢዩ ዳንኤል እግዚአብሔርን የምናስበልጥ፣ እግዚአብሔርን የምንፈራ፣ ለጾም የምናደላ ልጆች ልንሆን ይገባል እሺ ልጆች!

***የነቢዩ በረከት ይደርብን አሜን!***

**ምንጭ፡-** መጽሐፈ ስንክሳር፤

የትንቢተ ዳንኤል አንድምታ ትርጓሜ **መቅድም**፤ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፤መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ በመምህር ቸርነት አበበ፤ትንቢ ዳንኤል ፤ ከዘመነ ባቢሎን እስከ ዓለም ፍፃሜ ፣ በዲ/ን ዳንኤል ክብረት፤

# የመገናኛ ትዕይንት

ኪኑኪሩ ከአዲስ አበባ

አንድ ወዳጄ አዲስ አበባ ላይ ከመገናኛ ወደ ካዛንቺስ በታክሲ ስንጓዝ እየደጋገመ ‹‹ወይ ጉድ!›› ሲል እሰማዋለሁ፡፡ የሆነ አንዳች ነገር እንዳስተዋለ፣ ባየውም ነገር እየተብሰለሰለ መሆኑን ተረዳሁ፡፡ ቢችል ለሆነ ሰው የሚያስበውን፣ አእምሮውን ልቡናውን ሰቅዞ የያዘውን ጉዳይ የሚያዋየው ቢያገኝ ብዙ ሊል እንደሚችል ገመትኩ፡፡

ትንሽ ሄድ እንዳልን ይኸው ሰው አሁንም ደግሞ አፋን በእጁ ያዝ እያደረገ ‹‹የሚገርም ሀገር እየሆነ ነው›› አለ፡፡ ከአፉ የወጣውን ቃል ያስተዋለው አልመሰለኝም፡፡ አንድ ጊዜ ወደ መስተዋቱ፣ አንድ ጊዜ ወደ ተሳፋሪው ያማትራል፡፡ እኔም ይህ ሰው የልቡን ቢተነፍስ ዕረፍት ሊያገኝ እንደሚችል ስለተረዳሁ ደግሞ ከአፉ ቃል እስከሚወጣ እጠብቅ ጀመር፡፡

በድንገት የታክሲው ረዳት በር ሲከፍት አንድ ሙዳዬ ምጽዋት ይዘው ጥላ ያጠሉ ቄስ ወደ በሩ ቀረብ ብለው ቆም አሉ፤ ‹‹የቻላችሁትን ለቤተክርስቲያን ማሠሪያ ስጡ›› የሚሉ ይመስል ነበር፤ በዚያች ቅጽበት የሚችሉ ሁሉ ሳንቲሞቻቸውን ወጣ እያደረጉ ሰጡ፡፡ ከቄሱ ጀርባ ደግሞ ‹‹ኢየሱስን ተቀበሉ›› እያለ የሚጮኽ አንድ ወጣት ያንቧርቃል፡፡

ከአጠገቤ የሚብሰለሰለው ሰው ሳያውቀው ድምፁን ከፍ አድርጎ ‹‹እዚህም የመገናኛው ትዕይንት ሊቀጥል ነው እንዴ!?›› ሲል ሰማሁት፡፡ ይህንን አጋጣሚ ማባከን አልፈለግሁም፡፡ ‹‹የመገናኛ ትዕይንት ነው ያልከው?›› አልኩት ‹‹ታዲያስ! በጣም እኮ ይገርምሃል፤ በዚያ ብዙ ጊዜ እንዳለፍክ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ [አንገት አንገቴን እያየ] ሳይህ አንገትህ ላይ ክር አድርገኻል፤ ስለዚህ እንደልቤ ባወራህም እችላለሁ፡፡ መገናኛ ላይ በአራቱም አቅጣጫ አንስተኛ ሞንታርቦዎች የያዙ የጴንጤ ሰባኪዎች ያለማቋረጥ ሲጮኹ ታያለህ፤ ጩኸታቸው ወደ አዳራሾቻቸው ሰው ለመሳብ፤ የወንጌል አስተማሪ መስለው መታየት ነው፡፡ ከእነሱ በላይ የሚያስገርሙኝና የሚያሳዝኑኝ ግን በእኛ በኦርቶዶክሳውያን መለያ አልባሳት የተሰለፉ ቄስ እና መነኩሴ መስለው፣ ጥላ ይዘው ድምፅ ማጉሊያ ደቅነው በቤተክርስቲያን ስም ገንዘብ ስጡን እያሉ የሚለምኑ ሰዎች ታያለህ እነዚህም የእኛዎቹ መናፍቃኑ አጠገብ ቆመው ለልመና ይጮኻሉ፡፡ በጣም የሚያስገርምህ መነኩሴና ቄሶች ብቻ ሳይሆኑ ነጠላ የለበሱ ሌሎችም ሴቶችና ወንዶች ለልመና ተሰማርተዋል፡፡ በእርግጠኝነት የምነግርህ መናፍቃኑ በዚህ ደስተኛ ናቸው፡፡ የእኛዎቹ ሲለምኑ ሲታዩ እነዚያ ኢየሱስ ኢየሱስ ሲሉ እውነተኛ የወንጌል መምህራን መስለው ለመታየት ይጠቀሙበታል፡፡ እኔ ታዲያ ይህ ብቻ ሳይሆን የሚገርመኝ መገናኛ ላይ ያለ ትርምስን እና የድምፅ ብክለትን አደብ የሚያስገዛ አስተዳዳር መጥፋቱም ነው፡፡›› አለኝ፡፡

እኔም በሰማሁት ነገር ተደነቅሁ፤ በእርግጥም የመገናኛ የማታና ጠዋት ትዕይንት አስገራሚ ነው፡፡ በመገናኛ ብቻ የተወሰነ አይመስለኝም፡፡ ከምንም በላይ ግን ከሰውዬው ትዝብት የወሰድኩትና የእኔም ትዝብት ሆኖ ያገኘሁት የቤተ ክርስቲያናችን በር በጥቂት ርቀት ላይ የሚከወኑ መሰል ድርጊቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ መሄዱ ነው፡፡

የመገናኛ አደባባይ እጅግ ብዙ ሰዎች የሚመላለሱበት፣ የተጨናነቀ አደባባይ ነው፡፡ ብዙ ተመልካች ባለበት በዚህ አደባባይ ደግሞ መናፍቃን አድብተው ከመንጋው በጎችን ለመንጠቅ ከላይ ታዛቢው እንደገለጸው ልዩ ልዩ ደረጃ ባላቸው ድምፅ ማጉሊያዎች በቃልም ጭምር ከላይ ታች እያሉ ‹‹ወንጌል እናስተምራለን›› በሚል ስም ብዙዎችን እያደናገሩ ነው፡፡ በርካቶች ግራ በመጋባት፣ አንዳንዶችም ጆሮአቸውን ይዘው በማለፍ፣ አንዳንዶችም በቁጣ ስሜት እየተወራጩ፣ ሌሎች ደግሞ ግራ ተጋብተው ቆም ብለው በማስተዋል ትዕይንቱን ይታዘባሉ፡፡ መናፍቃኑም ደምፅ ማጉሊያ ብቻ ሳይሆን ጊታርና ክራር ይዘው በቡድን በቡድን በመሆን በመዝሙር መሰል ዘፈን የምእመናናን ቀልብ ለመሳብ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ የታተሙ በራሪ ወረቀቶች ይዘው ‹‹ተቀበሉን›› እያሉ ይታገላሉ፡፡ ይህ ሁሉ የጊዜያችን ድፍረት የዘመኑም የፍጻሜ ምልክት ሆኖ በትዕግሥት እየታየ ነው፡፡ መገናኛ የሥጋ መጠቀሚያ ቁሶቻችንን በሚሰርቁ ሌቦች የተጨናነቀ ነው፡፡ አሁን ደግሞ በጠራራ ፀሐይ ነፍሳችንን ሊሰርቁ በሚሹለከለኩ መናፍቃን እየተወረረ ነው፡፡

ከእነዚህ ትንኮሳዎች በላይ ግን እየጎዳን ያለው በእኛ ስም በገፍ የተሰማሩ ለማኞች ናቸው፡፡ ፀጉራቸውን አርዝመው፣ ቆዳቸውን ለብሰው፣ ‹‹ባሕታውያን ነን›› ብለው ለማስተማር የሚሞክሩ፤ ማንነታቸው

የማይታወቁ ሰዎችን እናያለን፡፡ ከዚያ ደግሞ ማይክሮፎን ይዘው ‹‹ላላለቀ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ማሠሪያ የሚሆን ድጋፍ ስጡን ›› እያሉ ጥላ ይዘው የሚለምኑም አሉ፡፡ ከዚያም አለፍ ብሎ የቅዱሳን ሥዕላትን ይዘው የሚለምኑ በርካታ ናቸው፡፡ ከዚያ አለፍ ብሎም ነጠላ የለበሱ ሁለት ሦስት ልጃገረዶች በጋራ በአንድ ደምፅ እየጮኹ ለሰንበት ትምህርት ቤታችን አዳራሽ ማሠሪያ እያሉ ይለምናሉ፡፡ ከዚያ አለፍ ሲባል ደግሞ መስቀል የያዙ ቀሳውስት መሬት ላይ ጨርቅና የተበታተነ ወረቀት ደርድረው በዝምታ ቆመው የሚሰጣቸውን ይጠባበቃሉ፡፡ ታዲያ ይህን ሁሉ ክዋኔ እያየ በዚያ ለሚያልፍ ኦርቶዶክሳዊ ወገን ምን ያህል ሕመም ይፈጥርበት ይሆን እላለሁ፡፡ ከእነዚህ ሥርዓት የሌላቸው ወገኖች ኦርቶዶክሳውያን ራሳቸውን ሊለዩ ይገባል፡፡ ሐዋርያው ‹‹ወንድሞች ሆይ፥ ከእኛ እንደ ተቀበለው ወግ ሳይሆን ያለ ሥርዓት ከሚሄድ ወንድም ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዛችኋለን፡፡ (፪ኛ ተሰሎ. ፫፥፮) ያለውን ቃል ማስተዋል ተገቢ ነው፡፡

ቤተክርስቲያን ምእመናንን የምታገኝበት የምትሰበስብበት የታወቀ ቅዱስ ሥፍራ አላት። በዚያ ምእመናን የሚፈልጉበትን አገልግሎት ይቀበላሉ፤ የቤተክርስቲያን አስተዳደርም ከምእመናን ለቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልገውን አገልግሎት ይጠይቃል፡፡ ታዲያ ስለምን የዓለም አደባባዮች ያስፈልጓታል፡፡ የተቀደሰውን ሥራ በተቀደሰው ስፍራ የማከናወን ሥርዓት የሚገባ ሥርዓት ነው፡፡ ለችግረኞች ምጽዋትን መጠየቅም ቢሆን በቅዱስ ቦታው ሲሆን ያምራል ይገባልም፤ መጽሐፍም ‹‹እግዚአብሔር በቅዱስ ቦታው ለድሀ አደጎች አባት፥ ለባልቴቶችም ዳኛ ነው፡፡›› (መዝ ፳፭፥፰) ማለቱን ልብ ይሏል፡፡

የቤተክርስቲያን አስተዳዳር የምእመናንን ዐሥራት በኩራትም ሆነ ሌሎች ድጋፎች መጠየቅ የሚገባቸው ክርስቲያኖች በሥርዓታቸው መሠረት በሚሰባሰቡበት የተለየ የታወቀ ስፍራ ላይ እንጂ በአደባባዮቹ በሚዘረጉ ሥርዓቶች አይደለም፡፡

የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳር ገንዘብ የሚሰበስበው ምእመናንን ለማገልገል ካለው ብርቱ ፍላጎት የተነሣ ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ የተቀበለችውን ተልእኮ ማስፈጸሚያ ነው፡፡ ነገር ግን በማይገቡ መንገዶች በየአደባባዮቹ በኦርቶዶክሳዊ መለያ የሚታዩ ተግባራት መንጋውን የሚበትኑ እንጂ የሚሰበስቡ አይሆኑም፡፡

በዚህ ረገድ የምንታዘበው ግን በዚህ ተግባር የተሰማሩ ሰዎችን ብቻ ሳይሆን በዚያ መንገድ እንዲቀጥሉ አላግባብ ገንዘባቸውን በመስጠት የሚያበረታቱ ምእመናንን ጭምር ነው፡፡ ምእመናን ከቤታቸው ሳይርቁ በሥርዓቱ መሠረት ለሚጠየቁት ድጋፍ ምላሽ ከመስጠት ባለፈ ገንዘባቸውን ላልታወቁና በሥርዓት ለማይመላለሱ ሰዎች በመስጠት ራሳቸውንና የቤተ ክርስቲያናቸውን ሥርዓትና ገጽታ እንዳይጎዱ መጠንቀቅ ይገባቸዋል፡፡ ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጥ ስጦታ ሁሉ ለእግዚአብሔር የሚሰጥ ስጦታ ነው፤ ስለዚህ በእግዚአብሔር ቤት ሲሰጥ ያማረ የሚገባም ነው፤ እርሱም ስጦታን በቤቱ የሚቀበል መሆኑን ሲናገር ‹‹ ‹‹ስጦታ ያመጡልኝ ዘንድ ለእስራኤል ልጆች ተናገር፤ በገዛ እጁ ሊሰጠኝ በልቡ ከሚያምረው ሰው ሁሉ መባ ተቀበሉ፡፡ (ዘጸ.፳፭፥፪) የሚሰጡትም የሚቀበሉትም አገልግሎታቸውን የሚፈጽሙት በእግዚአብሔር ቤት ነው፡፡ ከዚህ ሲያፈነግጥ ግን ፈተና መውለዱ የማይቀር ነው፡፡

ቃሉን ማስተማር የሚፈልጉ ወገኖችም ከአደባባዮች ይልቅ በታወቀ፣ በተገባ የተቀደሰ ዓውደ ምሕረት ሊያስተምሩ ይገባል እንጂ፤ በመናፍቃኑ አካሄድ፣ ወይም በፉክክር ወይም በከንቱ እልከኛነት በማይገባ አደባባይ ሥርዓት ባጣ መንገድ ለመስበክ መሞከር አያስደስትም ተገቢም አይደለም፡፡ ልበ አምላክ ዳዊት ‹‹በክፉዎች ምክር ያልሄደ፥ በኃጢአተኞችም መንገድ ያልቆመ፥… ምስጉን ነው›› (መዝ ፩፥፩) ያለውን እናስተውል፡፡

ከዚህ ባሻገር በየደረጃው ያለው የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳር እንዲህ ያሉ ያልተገቡ ትዕይንቶችን በቤተ ክርስቲያን ስም ሲስፋፉ እርምጃ ያለመውሰድ ችግር ይታይባቸዋል፡፡ የሚገሰጸውን መገሰጽ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ድርሻ ነው፡፡ ይህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ኃላፊነት ነው፤ ሐዋርያው ‹‹ቃሉን ስበክ፥ በጊዜውም አለጊዜውም ጽና፥ ፈጽመህ እየታገሥህና እያስተማርህ፥ ዝለፍና ገሥጽ፣ ምከርም፡፡ (፪ኛ ጢሞ ፬፥፪) ያለውን ማሰብ ይገባል፡፡ የሚመለከተው የመንግሥት አካል ከቤተ ክርስቲያን ኃላፊዎች ጋር በመነጋገር ሥርዓት ማስያዝ አለበት፡፡ የቤተ ክርስቲያን ችግር የሀገርም ችግር እንደሚሆን መዘንጋት የለበትምና፡፡

ቤተክርስቲያን አሁን በፈተና ውስጥ መሆኗ ይታወቃል ፤ ከውጪ ያሉ ፈተናዎች እየበዙ ሳለ ሥርዓት በማጣት ራሳቸው የቤተ ክርስቲያን ቤተሰቦች ደግሞ ፈተና የሚሆኑባት ከሆነ ነገሩን ያከፋዋል፡፡ አገልግሎቷም ፈጽሞ ይታወካል፡፡ አንዱን ስንገነባ ሌላው ይፈርስብናል፡፡ ስለዚህ ጥንቃቄ ይደረግ እንላለን፡፡

# «መስጠት ያስጨንቀኛል»

ውድ የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ አዘጋጆች እንደምን ከረማችሁ? በሕይወቴ ውስጥ ፈተና የሆነብን ለሰውም እናገረው ዘንድ የሚያሳቅቀኝን ምሥጢር ሳካፍላችሁ መፍትሔ የሚሆን መልስና ምክር ትሰጡኛላችሁ ብየ በማመን ነው፡፡

ከልጅነቴ ጀምሬ ዐሥራት በኲራት ስለመስጠት ስማር ኖሬያለሁ፡ ፡ ገንዘብ ኖሮኝ ይህንን ትእዛዝ በመፈጸም ሕይወቴን መልካም እንደማደርገው አስብ ነበር፡፡ ጊዜው ደርሶ እኔም አድጌ ለወግ መዓርግ በቅቼ ሥራ መያዝ ጀምርኩ፡፡ ነገር ግን ከመጀመሪያው ወር ደሞዜ ጀምሮ የገጠመኝ ፈተና የማገኘው ገንዘብ ያንን ለማድረግ እንደማይበቃኝ ማሰብ ነበር፡፡ ከዚያም ደሞዜ የተወሰነ ሲያድግ እንደምጀምር ባስብም ደሞዜ ባደገ መጠንም በምፈጥራቸው ልዩ ልዩ ፍላጎቶች የተነሣ ያለኝ ደሞዝ ማነሱ እንጂ ለቤተክርስቲያን አገልግሎት ለመስጠት የሚበቃኝን አድርጌ ማግን አልቻልኩም፡፡ አሁን ቤተሰብ መሥርቼ ከፍተኛና የተሻለ ደሞዝ ተከፋይም ሆኜ ባለቤቴም የተሻለ ደሞዝ ተከፋይ ሆና ሳለ ከዚህ ፈተና ግን አልዳንኩም፡፡ ለዐሥራት በኲራት የማወጣው ገንዘብ ኑሮዬን የሚናጋው ብዙ ጉዳትም የሚያመጣብኝ አድርጌ አስባለሁ፡፡ በባንክ ካስቀመትሁትም ገንዘብ አውጥቼ ለመስጠት አስብና ነገ አደርጋለሁ ብዬ ካቀድኩት ነገር የሚጎድልብኝ አድርጌ አምናለሁ፡፡ የእኔና የቤተሰቤ ተድላ ደስታ እንዲሁም የኑሮዬን ዋስትና የሚያናጋ እየመሰለኝ ይኸው ለዓመታት ለቤተ እግዚአብሔር ዐሥራት በኲራት ለመስጠት ድፍረት አጥቻለሁ፤ ለእግዚአብሔር ቤት ብቻ ሳይሆን ለድሆችም መስጠት ውስጤን ያስጨንቀዋል፤ ብሰጥ እንኳን እየተጨነቅሁ ነው፤ ምን ይሻለኛል ምከሩኝ፡፡

ውድ ጠያቂያችን፦ ሐሳብዎን በዝርዝር ጽፈው ዝግጅት ክፍላችን ለተጨነቁበት ነገር ምላሽ እንዲሰጥዎ በመጋበዝዎ ከልብ እናመሰግናለን፡ የእርስዎ ጥያቄ ምናልባትም የእርስዎ ብቻ ሳይሆን የሌሎችም የብዙዎች ጥያቄ ሊሆን ስለሚችል ለእርስዎ በምንሰጠው ምላሽ ሌሎችንም ለማገዝ እየሞከርን እንደሆነ ይሰማናል፡፡ በዚህ ዘመን በዚህ ዓለም አድራጊ ፈጣሪ ሆኖ እየታየ ያለው ገንዘብ መሆኑን በቀላሉ በእያንዳንዳችን ሕይወት ውስጥ ከሚፈጠረው ፈተና መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ አድራጊ ፈጣሪነት የሚሰማን ግን በእግዚአብሔር ላይ ያለ እምነታችን እየተሸረሸረ በመምጣቱ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ለዓለም ያለን ፍቅር በየጊዜው እየጨመረ በመምጣቱ በምኞት ታስረን ስላለን ነው፡፡

ውድ ጠያቂያችን፦ እርስዎ እንዳሉት በአሁን ዘመን ሰዎች ለሕይወታቸው የሚያስፈልገውን ነገር የሰጠን ገንዘብ ነው ብለው ማመናቸው አስገራሚ ላይሆን ይችላል፤ አስቀድሞም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በትምህርቱ ገንዘብን በሰዎች ሕይወት ውስጥ ፈተና ሆኖ ሊሠለጥን የሚችል ወጥመድ መሆኑን ነግሮናል፡፡ ሰዎች የመኖር ዋስትናቸው፣ የደስታቸውም ምንጭ ገንዘብ ነው ብሎ በማሰብ ይፈተናሉ፡፡ ከምንም በላይ የማይዘነጋው ታላቁ እውነታ ግን ሰዎች ገንዘብ ለማግኘት የሚያስችላቸውን መሠረታዊ ሁለንተና የሰጣቸው እግዚአብሔር መሆኑን መዘንጋታቸው ነው፡፡

የሚያስፈልገንን ለማግኘት የሚፈቅደው እግዚአብሔር ነው፡፡ በዚያም መጠቀምን የሚፈቅደው እርሱ ነው፡፡ ያገኘነውን ነገር በራሳችን ብቻ እንዳገኘነው እያሰቡ መመካት እጅግ ለነፍሳችን ወጥምድ ነው፡፡ ሐዋርያው ‹‹በአሁኑ ዘመን ባለ ጠጎች የሆኑት የትዕቢትን ነገር እንዳያስቡ፥ ደስም እንዲለን ሁሉን አትርፎ በሚሰጠን በሕያው እግዚአብሔር እንጂ በሚያልፍ ባለ ጠግነት ተስፋ እንዳያደርጉ እዘዛቸው፡፡ ›› (፩ኛ ጢሞ ፮÷ ፲፯) ብሏል፡፡

ለሁሉም ነገር ተራዳኢው እግዚአብሔር ነው፡፡ በዚህ ዓለም እንድንመላለስ ሕይወትን የሰጠን ገንዘብ ሳይሆን እግዚአብሔር ነው፡፡ በዚህ ዓለም ስንመላለስ ወጥተን ወርደን ሠርተን የምናገኝበትን ዕውቀት ክህሎት የምንላበስበትን ችሎታ ያደለን እግዚአብሔር ነው፡፡ ባዘጋጀልን የተፈጥሮ ሥርዓት ፀሐዩን በቀን፣ ጨረቃን ከዋክብትን በሌሊት አሠልጥኖ፣ ዝናቡን በክረምት ፀሐዩን በበጋ አብዝቶ በመስጠት ኑሮአችንን የሚያስምርልን እግዚአብሔር ነው፤ ጤናም ሰጥቶ የሚያውል የሚያሳድር እርሱ ነው፡፡ የምናይበትን ዓይን፣ የምንሮጥበትን እግር፣ የምንሰማበትን ጆሮ፣ የምንዳስስበትን እጅ አሳምሮ ፈጥሮ የሚሰጠን በዚህ ዓለም ሊኖረን የሚገባውን አብዝተን አምልተን መያዝ የምንችልበትን ጸጋ አድሎን ነው፡፡ ይህንን አለማመን ጠያቂያችን ያነሡት የኑሮ ዋስትና ገንዘብ ብቻ እንደሆነ ወደማሰብ ያመራል፡፡ የእምነት ጉድለት ሕይወትን ያናጋል፡፡ ኢዮብ ‹‹ወርቅን ተስፋ አድርጌ፥ ጥሩውንም ወርቅ፦ በአንተ እታመናለሁ ብዬ እንደ ሆነ፤ ... ልዑል እግዚአብሔርን በካድሁ ነበርና፤ ይህ ደግሞ ፈራጆች የሚቀጡበት በደል በሆነ ነበር፡፡›› (ኢዮ. ፴፩፥፴፬) ብሏል፡፡

የሚያምኑ ግን ብዙ ገንዘብ፣ ብዙም ንብረት፣ ከፍተኛ ሥልጣን ታላቅ ዝናም ቢኖራቸው ከእግዚአብሔር መሆኑን በማመን ቢያንስ በአንደበታቸው ያመሰግኑታል፡፡ ክብርም ብልጽግናም በዝቶለት የነበረው ልበ አምላክ ነቢዩ ዳዊት ለእንዲህ ያሉ ያመኑ ደጎች ምሳሌ ሊሆን የሚችል ቃሉን እናስታወስ፤ ‹‹ሁሉ ከአንተ ዘንድ ነውና፥ ከእጅህም የተቀበልነውን ሰጥተንሃልና ይህን ያህል ችለን ልናቀርብልህ እኔ ማን ነኝ? ሕዝቤስ ማን ነው? (፩ኛ ዜና ፳፱፥፲፬) ብሏል፡፡

ሌላው ወሳኝ መረዳት የሚገባዎት ነጥብ በገንዘብ ላይ ያልዎትን አደገኛ መተማመን ነው፤ ገንዘብ የሚታመን ወዳጅ አይደለም፡፡ የሚታመን የምንጊዜም መመኪያ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ‹‹የማወጣው ገንዘብ ኑሮዬን የሚያናጋው፣ ብዙ ጉዳትም የሚያመጣብኝ አድርጌ አስባለሁ፡፡›› ያሉት ከባዱ የሕይወትዎ ፈተና ነው፡፡ አስቀድመን በጠቀስነው በሐዋርያው ቃል ‹‹በሚያልፍ ባለ ጠግነት..›› የተባለውን ማሰብ ተገቢ ነው፡፡ ትንሽም ይሁን ብዙ የነገ ሕይወታችን ዋስትና ገንዘብ ነው ብሎ ማመን ነፍሳችንን የሚያጠፋት ወጥመድ ነው፤ ጌታ ‹‹ገንዘብ ላላቸው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት እንዴት ጭንቅ ይሆናል›› ያለው ይህንኑ አስተሳሰብ ነው፡፡ (ማር ፲፥፳፫) አስቀድሞም ጠቢቡ ሰሎሞን ‹‹በባለጠግነቱ የሚተማመን ሰው ይወድቃል፤...›› (ምሳ ፲፩፥ ፳፰) ያለውን ቃል ማሰብ ያስፈልጋል፡፡

ውድ ጠያቂያችን፦ ‹‹የእኔና የቤተሰቤን ደስታ እንዲሁም የኑሮ ዋስትና የሚያናጋ እየመሰለኝ›› ያሉትም በክርስቲያናዊ ሐሳብ መታረቅ ያለበት ነው፡፡ ሁላችንም ክርስቲያኖች ማሰብ ያለብን የደስታችን፣ ተድላችን ምንጭ እግዚአብሔር መሆኑን ነው፡፡ ክርስቲያኖች በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ለክርስቶስ አድረው ያላቸውን ሁሉ እየሰጡ ከእግዚአብሔር ጋር መሆን ብቻ ከፍተኛው የደስታቸው ምንጭ ነበር፤ ደስታ የሚሰጠው ለእግዚአብሔር እና ለድሆቹ ገንዘብን በመንፈግ ሳይሆን በመስጠት ነው፡፡ በሐዋርያት ዘመን ስለነበረው ሕይወት መጽሐፍ ሲነግረንም ‹‹በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቈረሱ፥ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር፤(የሐዋ ፪፥፵፮) ይለናል፡፡

ደስታ የሚገኘው ከእግዚአብሔር ጋር በመሆን ነው፤ መልካምን ነገር ሁሉ በማድረግ ነው፤ በጽድቅ ሥራ ሁሉ በመተባባር ነው፡፡ ገንዘብ የሚገዛው ነገር ሁሉ ለደስታ ምንጭነት ዋስትና የሚሰጥ አይደለም፡፡ በስስት በንፉግነት ውስጥ የሚሰፍነው ጭንቀት ነው፤ የኀሊና ወቀሳ ነው፤ ከእግዚአብሔር ጋር መጣላት ነው፡፡ ከዚህ ይልቅ በሥርዓት እየኖሩ በድህነት ውስጥ ያለ ደስታ ይሻላል፡፡ ጠቢቡም ‹‹ጥል ባለበት ዘንድ እርድ ከሞላበት ቤት በጸጥታ ደረቅ ቍራሽ ይሻላል፡፡›› (ምሳ ፲፯፥፩) ያለው ይህንኑ ነው፡፡

ለደስታ ምንጭነት የምንተማመንበትን ሀብት ንብረት ድንገት ልናጣው እንደምንችል ዛሬ፣ ዛሬ በሀገራችንና በዓለም ያሉ ሁኔታዎች እንኳን ያስረዱናል፡፡ የሚያኖረው ፍቅር ሰላም እንጂ ገንዘብ አይደለም፡፡ እነዚህ ደግሞ የሚገኙት ከእግዚአብሔር ነው፡፡ ሀብት ንብረት ግን የሚያልፉ የሚጠፉ እንደሆነ ሐዋርያው ‹‹ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘለዓለም ይኖራል፡፡›› (፩ኛ ዮሐ ፪፥፲፯) ያለው ቃል የሕይወት መመሪያችን መሆን ይገባዋል፡፡

ውድ ጠያቂችን፦ ከምንም በላይ ግን ‹‹ለእግዚአብሔር ቤት ብቻ ሳይሆን ለድሆችም መስጠት ውስጤን ያስጨንቀዋል፤ ብሰጥ እንኳን እየተጨነቅሁ ነው፤›› ያሉትን በውል ሊያጤኑት ይገባል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ‹‹እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ ይስጥ፥ በኀዘን ወይም በግድ አይደለም፡፡›› (፪ኛ ቆሮ ፱፥፯) ይለናል፡፡

ሰዎች ለእግዚአብሔር የሚሰጡት አምነው፣ ፈጣሪያቸውን መድኃኒታቸውን ወደውት ነው፤ ስሙ ለሚጠራበት ክብሩ ለሚነገርበት ቤቱ ለአገልግሎት አስፈላጊ እንደሆነ ታምኖ ይሰጣል እንጂ በጭንቀት አይደለም፡፡ ስጦታም ዕረፍት ሊሰጥዎት ይገባል እንጂ ሊጨነቁበት አይገባም፡፡ ለእግዚአብሔር ስንሰጥ እምነትና ፍቅራችን የሚገለጽበት ነው፡፡

ውድ ጠያቂያችን፦ ለድሆችም በልግስና ስንሰጥ ሰውን የመውደዳችን፣ አምላከ ነዳያን የምንለውን ኢየሱስ ክርስቶስን የማመናችን መገለጫ ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ስለመቄዶንያ ክርስቲያኖች ልግስና የመሰከረውንና ለቆሮንቶስ ምእመናን ያስተላላፈውን የሚከተለውን መልእክት አስተውሉ፦ ‹‹ወንድሞች ሆይ፥ ለመቄዶንያ አብያተ ክርስቲያናት የተሰጠውን የእግዚአብሔርን ጸጋ እነግራችኋለሁ፤ በብዙ መከራ ተፈትነው ሳሉ የደስታቸው ብዛትና የድህነታቸው ጥልቅነት የልግስናቸውን ባለ ጠግነት አብዝቶአል፤ እንደ ዓቅማቸው መጠን ከዓቅማቸውም የሚያልፍ እንኳ ወደው እንደ ሰጡ እመሰክርላቸዋለሁና፡፡ ለቅዱሳን በሆነው አገልግሎት እንዲተባበሩ ይህን ቸርነት በብዙ ልመና ከእኛ ይለምኑ ነበር፥ አስቀድመውም በእግዚአብሔር ፈቃድ ራሳቸውን ለጌታ ለእኛም ሰጡ እንጂ እንዳሰብን አይደለም፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በላከው መልእክቱ ‹‹ስለዚህም ቲቶ አስቀድሞ እንደ ጀመረ እንዲሁ ደግሞ ይህን ቸር ሥራ ደግሞ በእናንተ ዘንድ ሊፈጽም ለመንን፡፡ ነገር ግን በነገር ሁሉ፥ በእምነትና በቃል በዕውቀትም በትጋትም ሁሉ ለእኛም በፍቅራችሁ እንደ ተረፋችሁ፥ በዚህ ቸር ሥራ ደግሞ ትረፉ፡፡ ትእዛዝ እንደምሰጥ አልልም፥ ነገር ግን በሌሎች ትጋት በኩል የፍቅራችሁን እውነተኛነት ደግሞ ልመረምር እላለሁ፤የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ቸር ስጦታ አውቃችኋልና፤ ሀብታም ሲሆን፥ እናንተ በእርሱ ድህነት ባለ ጠጎች ትሆኑ ዘንድ ስለ እናንተ ድሀ ሆነ፡፡ በዚህም ነገር ምክር እሰጣለሁ፤ ከአምና ጀምራችሁ ለማድረግ ብቻ ያይደለ ነገር ግን ለማሰብ ደግሞ አስቀድማችሁ የጀመራችሁት ይህ ይጠቅማችኋልና፤ አሁንም ለማሰብ በጎ ፈቃድ እንደ ነበረ፥ እንዲሁ እንዳላችሁ መጠን መፈጸም ደግሞ ይሆን ዘንድ፥ ማድረጉን ደግሞ ፈጽሙ፡፡ በጎ ፈቃድ ቢኖር፥ እንዳለው መጠን የተወደደ ይሆናል እንጂ እንደሌለው መጠን አይደለም፡፡ ለሌሎች ዕረፍት ለእናንተም መከራ እንዲሆን አይደለም፥ ትክክል እንዲሆን ነው እንጂ፤ የእነርሱ ትርፍ ደግሞ የእናንተን ጒድለት እንዲሞላ በአሁኑ ጊዜ የእናንተ ትርፍ የእነርሱን ጒድለት ይሙላ፤ በትክክል እንዲሆን፥ እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፦ እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፦ ብዙ ያከማቸ አላተረፈም፥ ጥቂትም ያከማቸ አላጎደለም (፪ኛ ቆሮ ፰፥፩-፲፬) ይላል፡፡

የቅዱስ ጳውሎስ ምክር በፍቅር እንድንሰጥ ማሰብ ብቻ ሳይሆን ማድረግ እንድንለምድ፣ ስንሰጥ በልግስና ያለጭንቀት እንድንሰጥ ነው፡፡ጠያቂችን ሊረዱት የሚያስፈልገው ሌላው ቁም ነገር እግዚአብሔር ገንዘብን የሚሰጠው መልካም እንድንሠራበት ስንሠራበት ደግሞ እናጣዋለን ብለን ሳይሆን ይባረክልናል ብለን በማመንም ነው፡፡ ጌታችን ‹‹እኔም እላችኋለሁ፥ የዓመፃ ገንዘብ ሲያልቅ በዘለዓለም ቤቶች እንዲቀበሉአችሁ፥ በእርሱ ወዳጆችን ለራሳችሁ አድርጉ፡፡›› ብሏል፡፡ (ሉቃ፲፮፥ ፱) በአቅማችን ለእግዚአብሔር ቤት እንደሥርዓቱ ብንሰጥ፣ ድሆችንም በአቅማችን የቸርነት ሥራ ብንሠራላቸው ለራሳችን ክብር ያለው ዘለዓለማዊ ዋጋን በሰማይ እናከማቻለን፡፡

ገንዘባችን በመስጠታችን ይጎድልብናል ብሎ ማሰብ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ከእምነት ጉድለትና ካለማስተዋል የሚመነጭ ይሆናል፡፡ ገንዘባችንን በመስጠታችን እግዚአብሔር በብዙ መንገድ እንደሚባርክልን ማሰብ ማማን ያስፈልጋል፡፡ በስስታችን /በከንቱ ገንዘብ በማከማቸታችን ደግሞ የሚያሳጣንን ሌላ ብዙ ነገር ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡

‹‹እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ ይስጥ፥ በኀዘን ወይም በግድ አይደለም፡፡ ‹‹ለምስኪኖች ሰጠ፥ ጽድቁ ለዘለዓለም ይኖራል ተብሎ እንደ ተጻፈ፥ እግዚአብሔር፥ ሁል ጊዜ በነገር ሁሉ ብቃትን አግኝታችሁ ለበጎ ሥራ ትበዙ ዘንድ፥ ጸጋን ሁሉ ሊያበዛላችሁ ይችላል፡፡›› (፪ኛቆሮ ፱፥፱) እንደተባለ፤ በመስጠታችን አብዝቶ ይሰጠናል እንጂ አያጎድልብንም ብሎ ማመን ለክርስቲያን የሚገባ ነው እንላለን፡፡

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*